በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

# በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004ዓ.ም ከታተሙት የተማሪዉ መጻሕፍት ጋር ያላቸዉ የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ

በ

ግዛዉ ዓለሙ

ነሐሴ 2008

ጅማ ኢትዮጵያ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

# በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና 10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004ዓ.ም ከታተሙት የተማሪዉ መጻሕፍት ጋር ያላቸው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ

በ

ግዛዉ ዓለሙ

ዋና አማካሪ አብይ አሰፋ ( ዶ/ር)

ረዳት አቶ መሐመድ ጀማል

ነሐሴ 2008

ጅማ ኢትዮጵያ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | | |
|---|---|---|
| --------------------------- | ---------------------- | ----------------- |
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ---------------------------- | ---------------------- | ------------------- |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ------------------------------ | ----------------------- | --------------------- |
| ፈታኝ | ቀን | ፊረማ |

## ማረጋገጫ

በ2001 ዓ.ም የተዘጋጀው የ9ኛና 10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት በ2004 ዓ.ም ከታተመው የተማሪ መጽሐፍ ጋር ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬን ያስቀመጥኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ጽሑፎች ምንጮች በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ግዛው ዓለሙ

ፊርማ -----------

ጅማ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ጥናቱ አስፈላጊ ማሻሻያ የተደረገለት በመሆኑ ገቢ ይሁን፡፡

የአማካሪ ስም አቢይ አሰፋ (ዶ/ር)

ፊርማ -------------

ቀን --------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ጤናና ዕድሜውን ሰጥቶኝ ለዚህ ደረጃ እንድበቃ ያደረገኝ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡በመቀጠልም ይህንን ጥናት ስሰራ ውድ የሥራ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ሙያዊ እገዛቸውን ላደረጉልኝ ለዶ/ር አቢይ አሰፋና ለአቶ መሐመድ ጀማል ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡

በተጨማሪም ሁሉንም የቤት ውስጥ ጫና ተቋቁማ ለዚህ ደረጃ እንድበቃ ከጎኔ በመሆን ሁሌም ሳትታክት ላበረታታችኝ ውድ ባለቤቴ ወ/ሮ ምንትዋብ ወለላና ልጆቼ መቅድምና ህላዊ በልቤ ልዩ ሥፍራና ክብር አላቸው፡፡

በመጨረሻም የተለያዩ መረጃዎችን በማቀበል ለተባበሩኝ በሞራል በማቴርያልና በሀሳብ ላልተለዩኝ ውድ ጓደኞቼ በተለይም ለብዙወርቅ፣ ለከድርና ለሌሎች ወዳጆቼ ሁሉ ላቅ ያለ ምስጋና አለኝ፡፡

## የይዘት ማውጫ ገጽ


ምስጋና ---------------------------------------------------------------------- i

የይዘት ማውጫ ----------------------------------------------------------------- ii

የሠንጠረዥ ማውጫ -------------------------------------------------------------- v

አጠቃሎ --------------------------------------------------------------------------- vi

ምእራፍ አንድ

1.1 የጥናቱ ዳራ----------------------------------------------------------------- 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት-------------------------------------------------- 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ--------------------------------------------------------------- 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ------------------------------------------------------------ 4

1.5 የጥናቱ ክልል---------------------------------------------------------------- 5

ምእራፍ ሁለት

2.1 ክለሳ ድርሳናት--------------------------------------------------------------- 6

2.1.1 ስርአተ ትምህርት ምነድነው---------------------------------------------6

2.1.2 የመርሃ ትምህርት ምንነት---------------------------------------------- 7

2.1.2 የመርሃ ትምህርት ጠቀሜታ-------------------------------------------- 9

2.1.3 የቋንቋ መርሃ ትምህርት አይነቶች------------------------------------ 12

2.1.3.1 ሰዋስዋዊ መርሃ ትምህርት------------------------------------------ 12

2.1.3.2 ግልጋሎታዊ/እሳቤያዊ መርሃ ትምህርት---------------------------- 12

2.1.3.3 ቅደም ተከተላዊ መርሃ ትምህርት---------------------------------- 13

2.1.3.4 ይዘት ተኮር መርሃ ትምህርት--------------------------------------- 14

2.1.4 የቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘት አመራረጥ-------------------------- 16

2.1.5 የቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት------------------------- 16

2.1.6 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ------------------------------------------------- 17

2.1.6.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት------------------------------------ 17

2.1.6.2 የቋንቋ መማሪ መጽሐፍ ጠቀሜታ ----------------------------------- 18

2.1.6.3 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት አይነቶች------------------------------ 18

2.1.6.3.1 ጥንታዊ የመማሪያ መጽሐፍት ------------------------------------ 19

2.1.6.3.2. የጥንታዊ መማሪያ መጽሐፍት ባህርያት---------------------- 19

2.1.6.3.3 ተግባቦታዊ የመማሪያ መጽሐፍት---------------------------------- 20

2.1.7 የቋንቋ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍት ተጣጥሞሽ----- 21

2.1.8 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት--------------------------------------------- 22

**ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ዘዴ**

3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች--------------------------------------------------- 26

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች------------------------------------------ 26

3.2.1 የሰነድ ምርመራ------------------------------------------------------- 26

3.2.2 ቃለ መጠይቅ------------------------------------------------------------ 27

3.2.3የትምህርት ቤት ናሙና መረጣ --------------------------------------- 27

3.2.4 የመረጃ ትንተና------------------------------------------------------------ 28

**ምዕራፍአራት ፡-የውጤት ትንተና**

4.1 የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች

አጭር መግለጫ----------------------------------------------------------------- 29

4.1.1 የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የቋንቋ መርሃ ትምህርቶች የይዘት

አመራረጥ-------------------------------------------------------------- 30

4.1.2 በመርሃ ትምህርቱ የተቀረጹትን ዓላማዎች ከማሳካት አንጻር------30

4.1.3 መርሃ ትምህርቱ የተማሪዎችን ሁኔታ ግምት ዉስጥ ከማስገባት አንጻር----------------------------------------------------------------------- 40

4.1.4 የመርሃ ትምህርቱ የይዘት አደረጃጀት---------------------------------44

4.1.4.1 መርሃ ትምህርቱ ተከታታይነትን ከመከተል አንጻር------------ 44

4.1.4.2 መርሃ ትምህርቱ ተለጣጣቂነትን ከመከተል አንጻር-------------- 50

4.2. የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች አመራረጥ----------------------------53

4.2.1.1 የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሰረት ከማድረግ አንጻር---------------------------------54

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ ----------------------------------------------------------------- 59

5.2 አስተያየት ----------------------------------------------------------------- 60

V. ዋቢ መጽሐፍት------------------------------------------------------------- 61

አባሪዎች

አባሪ አንድ- የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማዎች

አባሪ ሁለት- የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማዎች

አባሪ ሦስት- የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘቶች

አባሪ አራት- የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘቶች

አባሪ አምስት- ለመምህራን ቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአገር አቀፍ ደረጃ በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች በ2004 ዓ.ም ከታተሙት የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ጋር ያላቸውን የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሆነው የሰነድ ምርመራ ሲሆን በሰነድነት የሚመረመረውም የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍት ናቸው፡፡በተጨማሪም በደጋፊነት በ9ኛና 10ኛ ክፍል ቋንቋውን ለሚያስተምሩ መምህራን ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የተገኙ መረጃዎችን በገላጭ የምርምር ዘዴ ስር የሚታቀፈውን ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ትንታኔ አድርጓል፡፡

*በዚሁ መሠረት የመርሀ ትምህርቶቹንና የመማሪያ መፃሕፍቱን ይዘቶች ከይዘት አመራረጥ እና አደረጃጀት መርሆች አንጻር እንዲሁም በመርሀ ትምህርቶቹ እና በመማሪያ መጽሐፍቱ መካከል ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ ተፈትሿል፡፡ዓላማውን ለማሳካት በዋናነት የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለገለው የሰነድ ምርመራ ሲሆን በደጋፊነትም በ9ኛና 10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ የተገኘው መረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ውጤቱ እንደሚያመለክተው የመማሪያ መፃሕፍቱ ጥቂት ይዘቶች በስተቀር የመርሀ ትምህርቶቹን ዓላማ መሰረት ያደረጉና የተጣጣሙ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የተመረጡት ይዘቶች የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ያገናዘቡ ከመሆናቸውም በላይ የመርሀ ትምህርቶቹ እና የመማሪያ መጽሐፍቱ የይዘቶች አደረጃጀት በአብዛኛው የክብደት ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአንድ አገር የስልጣኔ እድገት ዋነኛ ማሳያ ከሆኑት ነገሮች መካከል ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ትምህርት ነው። ያለ ትምህርት መሳሪያነት ያደገ አገር የለም ማለት ይቻላል። ይህም በመሆኑ አገሮች ለዚህ ልዩ ትኩረት በመስጠት ትምህርቱ የሚሻሻልበትን መንገድ በመቀየስና ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በማፍሰስ የምርምር ስራን በማካሄድ የትምህርት ስርአታቸውን በመፈተሽ በመገምገምና በማረም የተሻለ አሰራር ጥራት እንዲሰፍን እየሰሩ ይገኛል።

በዚሁ መሰረት ከትምህርት ፖሊሲ ቀረጻ እስከ ተማሪ መማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ድረስ ያሉት ሁሉ ደረጃ በደረጃ እየተፈተሹና እየተሻሻላሉ ሲሰራባቸዉ የቆየ ሲሆን ወደፊትም ይሰራባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ከሚሻሻሉት ደረጃዎች አንዱ የመርሃ ትምህርት ነው፡፡ Willis (1990) የመርሃ ትምህርትን ጠቀሜታ አስመልክተው "መርሃ ትምህርት ምን መማር እንዳለብንና በምን ዘዴ መማር እንዳለብን የሚገልጽ ሲሆን የመርሃ ትምህርት ዓላማ የቋንቋን ትምህርት ይዘት፣አደረጃጀትና አካሄድ ትርጉም ባለው መልኩ አዋቅሮ የሚይዝ መሳሪያ ነው፡፡" በማለት ገልጸዋል፡፡ መርሃ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት መንጭቶ የተማሪው መጽሐፍ ዓላማና ይዘት የሚወስን ቁልፍ የትምህርት አካሄድ መመሪያ ነው፡፡

በሃገራችን ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረው በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት እንደነበር ታሪክ ያወሳል፡፡ይሁን እንጂ የትምህርት ሥርዓቱ የኢትዮጵያን ባህልና ቋንቋ ያማከለ ሳይሆን በተለያዩ የውጭ አገራት የትምህርት ሥርዓት ተጽዕኖ ስር እንደነበረ Alemayehu (2012) በጻፉት ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ በተለይም እነ ፈረንሳይ፣ጣልያን፣ እንግሊዝና አሜሪካ በቀየሱልን የትምህርት ስርዓት ስንመራ እንደነበር አስፍረዋል፡፡ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን፣ ዘመናዊ ትምህርት ትጀምር ይባል እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠት የተጀመረው ግን ዘግይቶ እንደሆነ አኚሁ ምሁር በጽሁፋቸው ጠቅሰዋል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የሃገራችን ስርዓተ ትምህርት በጽሁፍ መልክ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ የዋለዉ በ1947/48 ኢትዮጵያዉያን የተሳተፉበትና ከውጭ አገር ሰዎች ተወጣጥቶ በተቋቋመ ኮሚቴ ነበር፡፡ይሁን እንጂ ሥርዓተ ትምህርቱ የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታን ያገናዘበ ሳይሆን ለጥቂት የገዢ መደቦች ፍላጎት ያደላ ነበር፡፡ይህ በጽሑፍ የቀረበዉ ስርዓተ ትምህርት ከ1948-1968 ዓ.ም መካከል ባሉት 20 ዓመታት ዉስጥ ብቻ ለሰባት ጊዜያት ተከልሶ ተዘጋጅቷል በማለት Alemayehu(2012)ያስረዳሉ፡፡

የሃገራችን ዘመናዊ ትምህርት በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ከቀረበበት ዘመን አንስቶ እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ የነበረዉ እንደ ሥርዓተ መንግስቱ አመለካከትና ፍልስፍና በየደረጃዉ እየተሻሻለና እያደገ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፣ አሁን ያለ የሃገራችን የፌደራል አስተዳደር የትምህርት ስርዓት ግን ከቀደሙት ስርዓተ ትምህርቶች በእጅጉ ተሻሽሎ

የሃገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ ዓላማዎች መሰረት ያደረገ ግልጽነትና ወጥነት ያለዉ የተማሪዉን አእምሯዊና ስነልቦናዊ ዕድገት አማክሎ የተዘጋጀ እንደሆነ እኝሁ ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ያስረዳሉ፡፡

ከትምህርት ፖሊሲው የመነጨው ሥርዓተ ትምህርት በየደረጃው ላሉት የክፍል ደረጃዎች በየትምህርት አይነቱ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅቶለት ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል።በዚሁ መሰረት የአማርኛ ቋንቋም የራሱ የሆነ መርሃ ትምህርት ተዘጋጅቶለት ትምህርቱ በተሳካ ሁኔታ በመሰጠት ላይ ቢሆንም በዝግጅት ገዜ በሚከሰቱ ስህተቶች ምክንያት ችግሮች እንደሚስተዋልባቸው አለም(1992) ያስረዳሉ፡፡

እነዚህም ችግሮች የዓላማና የይዘት አለመጣጣም፣ የይዘት አደረጃጀቱ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት መርህን ያለመከተል ችግር ጋር የተያያዙ፣ የተማሪዉን የባህርይ ለዉጥ ከመገንባት ሁኔታ አንጻር እንዲሁም ከሌሎች የመርሃ ትምህርቱ አቀራረብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ስህተቶች የመማር ማስተማሩን ስራ በተሳካ ሁኔታ ለማስተላለፍ አስቸጋሪ እንደሚያደርጉት በመግለጽ ችግሩን ለማስቀረት የትምህርት ባለሙያዎች መርሃ ትምህርቱን በየደረጃዉ እየፈተሹ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባቸው ያሳስባሉ፡፡

Willis (1990፣44) "የመርሃ ትምህርት፣የቋንቋ ትምህርት ዓላማና ይዘት በስርዓት ተቀነባብሮ የሚገለጽበት ትርጉም ያለዉ የስርዓተ ትምህርት አካል ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ምዕራፍ አላማ ተማሪዉ ምዕራፉን ተምሮ ካጠናቀቀ በኋላ የሚጎናጸፈዉን የባህርይ ለዉጥ የሚያመለክት ነው" ይላሉ። የተማሪዉን የባህሪ ለዉጥ ለመለካት ደግሞ ከአጠቃላይ የመርሃ ትምህርቱ ዓላማ የሚመነጩት ይዘቶች ከዝርዝር ይዘቶች ጋር ተጣጥሞሽ ሲኖራቸዉ ነው።

ታደሰና ሌሎች (2004፣103-104) "ማንኛዉም የትምህርት መርሃ ግብር የሚመራዉ በስርአት በተቀነባበሩ ዓላማዎች ነው፡፡...ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ለይዘት ምርጫቸው አደረጃጀት ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልጋል" በማለት የትምህርት ዓላማና ይዘት ምን ያህል ቁርኚት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ምሁራኑ ስለመርሃ ትምህርት ያሰፈሩትን መሠረት በማድረግ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ከተማሪው መማሪያ መጻሕፍት ጋር ያላቸው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ፣ የይዘት አደረጃጀት፣ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አንጻር ያለው አቀራረብ ለማየት ተሞክሯል፡፡

## 1.2 **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**

የዚህ ጥናት አጥኚ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማና ይዘት ከተማሪዉ መጽሐፍ ጋር ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ የሚለውን ርዕስ ለማጥናት ያነሳሳው፡-

※ በረዥም ጊዜ የማስተማር ልምዱ በማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ የተለያዩ ስህተቶች ሲገጥሙት የቆየ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ተነሳስቶ ስለፈጠረበት፣

※ አጥኚው ሊሰራው በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች በማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ወቅት ችግሮች እንዳሉ ስለሚያመለክቱ ችግሮቹ በባለሙያዎች እየተጠኑ መስተካከል እንደሚገባቸው ጥናቶቹ ስለሚያሳስቡ፣

※ አሁን እየተሰራባቸውና አገልግሎት እየሰጡ ባሉት መርሃ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ችግሮቹ ምን ያህል ተቀርፈው እንደተደራጁና እንደቀረቡ ለማሳየት ስለፈለገ ነው፡፡

## **1.3 የጥናቱ ዓላማ**

በ2001 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በቀረበዉ መርሃ ትምህርት ላይ ተመሥርቶ በ2004 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ላይ የሰፈሩ ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች በተማሪዉ መጻሕፍት ላይ ከቀረቡት ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ መፈተሸ ይሆናል፡፡ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

※የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ ከማሳካት አንጻር እንዴት ይታያሉ?

※ የመርሃ ትምህርቱ ዓላማና ይዘት ከመማሪያ መጻሕፍት የይዘት አደረጃጀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ምን ይመስላል?

※ በ9ኛና 10ኛ ክፍል የመማሪያ መጻሕፍትና መርሃ ትምህርቶች ውስጥ ያሉት ይዘቶች ምን ያህል ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አላቸው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል በዋነኛነት ከሚጠቀሱት መካከል የመርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡እነዚህ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ እያሉ ማጥናት ክፍተታቸዉ በቀጣዩ ህትመት ላይ እንዳይደገምና ተሟልቶ በጥንቃቄ እንዲዘጋጅ ይረዳል፡፡ይህ ጥናትም በ2001 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ የተዘጋጀዉ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004 ዓም በክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው የመማሪያ መጻሕፍት ጋር ያላቸው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ መፈተሽ በመሆኑ ጥናቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

※ በ9ኛና 10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ከዚህ ጥናት ዉጤት በሚያገኙት ፍንጭ መሠረት የመማር ማስተማር ሥራቸዉን እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፡፡

※ ለመርሃ ትምህርትና ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ደግሞ በዝግጅት ምዕራፍ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመጠቆም አደረጃጀታቸውን ደጋግመው እንዲከልሱና የማሻሻያ እርማት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

※ ለወደፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይና ተዛማጅ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች ፍንጭ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ክልል

ይህ ጥናት በ2001 ዓ.ም ተዘጋጅቶ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በውስጣቸው ከሚያቅፉት ነገሮች ማለትም የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ዓላማዎች፣ የቋንቋ ማስተማሪያ አዉደ ርዕስ፣ ይዘት፣ የክህሎት ብቃት፣ የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሳሪያ፣ ማጣቀሻና ግምገማ መካከል በሁለቱ ማለትም በዓላማና ይዘት ላይ ብቻ ያተኩራል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 ስርአተ ትምህርት ምንድነው?

በቀለና ሌሎች(2003፣4) Taba(1962) በመጥቀስ " ስርዓተ ትምህርት ተማሪው በትምህርት ቤት እንዲማረው የታቀደውን የትምህርት  አላማ ከግብ እንዲደርስ የሚመራ ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

Richard (2013፣7) ሥርአተ ትምህርት ለትምህርትንት የተመረጡትን ይዘቶች ቅርጽ በማስያዝና በማቀድ የመማር ማስተማር ስራ በተሳካ ሁኔታ ማስተላለፍ የሚያስችል ነው"በማለት የስርአተ ትምህርትን አገልግሎት ያስረዳሉ፡፡

ትምህርት ሚንሰቴር1994፣12) የኢትዮጵያ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ላይ ሥርአተ ትምህርትን እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡፡

1.ስርአተ ትምህርት በትምህርት ፖሊሲው አላማ ላይ ተመስርቶ የተማሪዎች ውጤታማነት የሚረጋገጥበት ፕሮፋይል ነው፣

2. ስርአተ ትምህርት መምህራን፣የትምህርት ባለሙያዎችና ትላልቅ ተቋማትን በማሳተፍ የትምህርት ፖሊሲው አላማ ስራ ላይ የሚውልበት ነው፡፡

3. ስርአተ ትምህርት የመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት በማዕከልና በክልል ደረጃ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው እንዲሁም የመማር ማስተማር ዘዴ የተማሪው ስነ ልቦናና ስርአተ ጾታ ላይ ተመስርቶ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ መዘጋጀቱ የሚረጋገጥበት ነው፡፡

4. ስርአተ ትምህርት የትምህርት ጥናትና ምርምር እንዲሁም ግምገማ የሚያያዙበትን ስልት በመቀየስና የተማሪው ተሳትፎ የሚጎለብትበት በተለያዩ የትምህርት እርከኖች በሚደረግ ስልጠናና ምርምር የህብረተሰቡን ፍላጎት አማክሎ ከተፈለገው ግብ ላይ የሚያደርስ ነው፡፡

ከላይ በምሁራኑም ሆነ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው የተገለጹት ንድፈ ሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳቦች ስለ ስርአተ ትምህርት ምንነትና አገልግሎት የሚያብራሩ ሲሆን ይህም ወደ ስራ ሊተረጎም የሚችለውየትምህርት ይዘቶችና ዓላማዎች በመርሃ ትምህርት ላይ በስርአት ተቀነባብረው በክፍል ውስጥ ሲሰጡ ነው፡፡

2.1.1 **መርሃ ትምህርት ምንድነው?**

ስለ መርሃ ትምህርት ምንነት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ይሁን እንጂ እነዚህ ብያኔዎች እንደ ምሁራኑ አመለካከትና አተያይ ልዩነት ስለሚታይባቸው አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ሊሰጠው አልቻለም፡፡

አለም (1992፣177) ጂንስ ዬልደን የተባለች ምሁር ዋቢ በማድረግ መርሃ ትምህርትን መግለጽ ቀላል እንዳልሆነ ጠቅሰው በሰሜን አሜሪካ "መርሃ ትምህርት የተሰኘው ክፍል ሥርዓተ ትምህርት ከሚለው ክፍል ጋር አቻ ተግባር የሚያከናውን ተደርጎ ሲታይ አንዱ አንዱን ተክቶ ማገልገል የሚችል መሆኑን ያመለክታል"ይላሉ፡፡በእንግሊዝ አገር ደግሞ "መርሃ ትምህርት እንደ አንድ የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ተደርጎ ይታያል" ይላሉ

ከላይ የመርሃ ትምህርትን አስመልክቶ ከተሰጠው ንድፈ ሀሳብ መረዳት የሚቻለዉ ሁለት አይነት አተያይ እንዳለ ነው፡፡ይሄውም አንደኛው አተያይ "መርሃ ትምህርት ከሥርዓተ ትምህርት ጋር አቻ ነው" የሚለውና ሁለተኛው አተያይ ደግሞ "መርሃ ትምህርትና ሥርዓተ ትምህርት የተለያዩ ናቸው" የሚለውን ሀሳብ የሚያራምዱ ናቸው (Yalden,1991)፡፡ ሁለቱንም ጎራዎች ስንመለከት በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚለያዩበት ነጥብ እንዳለ ሁሉ መርሃ ትምህርቶች ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ወሳኝ ናቸው ማለታቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡፡

Ur (1996፣177) "መርሃ ትምህርት በአንድ አጠቃላይ ትምህርት ሊጠቃለሉ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችን ለመተግበር ታቅዶ የሚዘጋጅ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ወይም መጽሄት ነው" በማለት ሰለመርሃ ትምህርት ምንነት ያስረዳል፡፡ አያይዞም "በአንድ በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ ተሰርቶ ለሚጠናቀቅ የሚዘጋጅ የራሱ የሆነ መግቢያ፣የይዘት ገጾችና የአርዕስት ማዉጫ አመልካች የሆኑ ነገሮችን ያካተተ አጠቃላይ መረጃ የያዘ ሲሆን ይህም መርሃ ትምህርት ይባላል" በማለት ይገልጻል፡፡

Nunan (1985፣5-6) ስለመርሃ ትምህርት ምንነት Yalden (1984፣14) ጠቅሶ "መርሃ ትምህርት፤በመርሃ ትምህርት ባለሙያዎች ተቀርጾ የቀረበ በመማሪያ ክፍል ዉስጥ

ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን የያዘ በተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ መሀከል ተግባቦት እንዲኖር የሚያገለግል መረጃ ነው" በማለት ያብራራሉ፡፡

Sari,Ifan.et,al (2014 ፣822) "በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የዓለም ሃገራት የቋንቋ ትምህርት

የሚዘጋጀው መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ ነው፡፡"ይህም ማለት የማስተማሪያ

መሳሪያዎች እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸውና በምን ዓይነት ዘዴ በክፍል ዉስጥ መጠቀም እንደሚገባ መርሃ ትምህርት ጠቋሚ መሆኑን ይገልጻል፡፡

Dubin እና Olshtain (1986፣33) ስለመርሃ ትምህርት ምንነትና ከስርዓተ ትምህርት ጋር ስላለለው ግንኙነት ሲገልጹ "ሁለቱም ጽንሰ ሀሳቦች ከትምህርት ዝግጅት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው በመካከላቸዉ ያለው ቁርኘት ጥብቅ ነው፡፡ ብዙዎች ምሁራን እንደሚያምኑት መርሃ ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ላይ ተመርኩዞ ይዘጋጃል፤የሥርዓተ ትምህርቱ አላማም በተግባር ይተረጎምበታል" ይላሉ፡፡

Wills (1990) "መርሃ ትምህርት ምን መማር እንዳለብንና በምን ዘዴ መማር እንዳለብን የሚገልጽ ሲሆን የመርሃ ትምህርት ዓላማ የቋንቋን ትምህርት ይዘት፣አደረጃጀትና አካሄድ ትርጉም ባለው መልኩ አዋቅሮ የሚይዝ የትምህርት መሳሪያ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

መርሃ ትምህርት ከስርአተ ትምህርት አንፃር ሲታይ ውስንነት ጎልቶ የሚታይበት ትምህርታዊ ሰነድ ነው:: ይህ ሰነድ ለመማር ማስተማሩ እንቅስቃሴ የሚረዳ ንድፍን ከተገቢ የትግበራ አቅጣጫ ጋር ያመለክታል (Brumfit:1984:8)::

በተጨማሪም መርሃ ትምህርት በክፍል ዉስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ክንውን የሚያጠናክር ተገቢ ዕቅድ የማደራጀቱን ተግባር የሚመራ ነው:: መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት አይነት ወይም የክፍል ደረጃ የሚሸፈን የትምህርት ርዕስ የሚገለፅበት ነው:: እያንዳንዱ በክፍል የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት የሚያስፈልገው የጊዜ ወሰን፣ የትምህርት አቀራረብ፣ ዘዴና ልምምድ የሚደረግበት ሂደት በማያሻማ መንገድ የሚቀርብበት ነው (Cunning Worth 1995:54-58)፡ ፡

በአጠቃላይ ከላይ ስለ መርሃ ትምህርት ምንነት የተሰጡት ብያኔዎች የተለያዩ ይምሰል እንጂ በመሠረተ ሀሳብ ደረጃ አንድ እንደሆኑ ፣አገልግሎታቸውም ለመማሪያ መጽሐፍት

ዝግጅት ቁልፍና እጅግ ወሳኝ መሆናቸው እንዲሁም የመማር ማስተማር ሥራ ስኬታማ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ከምሁራኑ ንድፈ ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.2 የመርሃ ትምህርት ጠቀሜታ

መርሃ ትምህርት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ይገልጻሉ፡፡Ur (1996፣177) "መርሃ ትምህርት ለመምህራን ከሚሰጠው ጠቀሜታ ባሻገር ተያያዥነት ላላቸው ሀላፊዎች፣ለጥናት አድራጊዎች፣ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ጠቀሜታ አለው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

Yalden (1987:86) " መርሃ ትምህርት መምህሩ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሃላፊነቱን በትክክል ለመወጣት እንድችል የሚያግዝ፣ አቅጣጫን የሚመራና ለደረጃው የተዘጋጀውን ይዘት ተማሪዎች ዘንድ ለማድረስ የሚያስችለው የሥራ መመሪያ ነው:: በመሆኑም መርሃ ትምህርት የተማሪውን ፍላጎት በክፍል ውስጥ ከሚካሄደው ትምህርት ክንውን ጋር እንዲጣጣም የሚያስችል በመሆኑ ትምህርታዊ ግልጋሎትን ለማህበረሰቡ ለማበርከት ሃላፊነቱን የሚወጣበት ተደርጎ መታየት ይኖርበታል" ይላሉ፡፡

Brumfit (1984:15) መርሃ ትምህርት በክፍል ውስጥ ክንውን በምን አይነት መንገድ መዘጋጀት እንዳለበት ሲገልጽ "መርሃ ትምህርት ከመነሻ እስከ መድረሻ ድረስ ያለው የትምህርት ሂደት በዕቅድና በስርአት እንዲከናወን ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ቁጥጥሩ የሚካሄደው የትምህርት መርሃ ግብር አስፈፃሚዎች የሆኑት መምህራን ናቸው:: የትምህርት ተቋሙ የሚገኝበት ህብረተሰብ የሚከተለው ፍልስፍናም አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም:: ላቅ ያለ ዲሞክራሲያዊ ስርአት በሰፈነበት ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ተቋሞች የመርሃ ትምህርቱ ተግባራዊነት እንደ ግዴታ የሚቆጠር ሳይሆን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስምምነት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

Parks and Harris (2002፣56) መርሃ ትምህርት በአንድ ክፍል ዉስጥ የታቀዱ የትምህርት ይዘቶች በግልጽና በተሟላ ሁኔታ የሚሰፍርበት በመሆኑ የትምህርት ምዕራፎችና ምዕራፎቹን ለመሸፈን የሚወስደው ጊዜ የሚወሰንበት፣ለክፍሉ የመማሪያ መጽሐፍት ይዘቶች የሚመረጡበት ፣ የሚወሰኑበትና ቅደም ተከተላቸው የሚደራጅበት የማስተማሪያ መሳሪያ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

አለም (1992፣180-181) Hutchinson (1987)፣ Dubin እና Olshtain (1986) በመጥቀስ የመርሃ ትምህርት ጠቀሜታ እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

1.ቋንቋ ዉስብስብና ረቂቅ የሆነ የመግባቢያ መሳሪያ በመሆኑ ይህን ረቂቅና ዉስብስብየመግባቢያ መሳሪያ በቀላሉ ማስተማር ይቻላል ተብሎ በደፈናው መገመት የዋህነት ነው፡፡ይህን ረቂቅና ዉስብስብ የመግባቢያመሳሪያ ተማሪው በአግባቡ እንዲማር፤መምህሩም በአግባቡ እንዲያስተምር ለማድረግ ረቂቁና ውስብስቡ ቋንቋ በጥልቀት ተመርምሮ ደረጃ በደረጃ ለትምህርት ሊቀርብ በሚችልበት መልኩ ተሸንሽኖ መቀመጥ አለበት፡፡እንዲህም ሆኖ ሲቀመጥ የመማሪያ መጽሐፍን ለማዘጋጀትና ሌሎችንም የማስተማሪያ መረጃዎችንም ለማሰናዳት እድል ይሰጣል፡፡ለዚህም የመርሃ ትምህርትመኖር ግድ ነው፡፡

2.መርሃ ትምህርቱ የቋንቋ ትምህርት አቅድን ከመነሻው እስከ መድረሻው ጥርት አድርጎ ስለሚያሳይ የቋንቋውን የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በተመለከተ መምህሩም ሆነ ተማሪዎችበራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍ እንዲል ያግዛል፡፡

3.መርሃ ትምህርቱ የቋንቋ ትምህርት ሂደት አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት ግብ ብቻ የሚጠቁም ሳይሆን ወደ ግብ መድረሻው መንገድ ላይምተማሪዎቹና መምህራኑ እንዴት

መራመድ እንዳለባቸው ጭምር የሚጠቁም ነው፡፡

4.መርሃ ትምህርት መምህራን ቋንቋን ለምን እንደሚያስተምሩትና ተማሪዎች ለምን ቋንቋን እንደሚማሩት በተዘዋዋሪ የሚገልጽ፣ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በየትኛዉ የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተዉ መማር እንዳለባቸዉ የሚያመለክት መሪ ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ነው፡፡

5.መርሃ ትምህርት የማስተማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀትና የማስተማሪያ መሳሪያ ለመምረጥየሚያገለግሉ መስፈርቶችን የሚይዝ ብቻም ሳይሆን ትኩረት ሊያገኝ የሚገባውንየመልመጃ አይነትም ጭምር በመጠቆም ለቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

6.መርሃ ትምህርት በአንድ ትምህርት ቤት፣በአንድ ከተማ፣በአንድ ክፍለ ሃገር፣ ብሎም በሃገርአቀፍ ደረጃ ያልተኻ ኘረጎረ አንድ ወጥ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ ትምህርት ለመስጠት ዋናና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

7.መርሃ ትምህርት በድህረ ቋንቋ ትምህርት ለሚደረገዉ ግምገማ መሰረትና መነሻ ሆኖስለሚያገለግል የቋንቋው ትምህርት ሲጠቃለል ለሚደረገው የግምገማ ወይም የምዘና ሂደትየመመዘኛውን ወይም የመገምገሚያውን መስፈርት በመጠቆም ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር ከቀረበው ማብራሪያ እንደምንረዳው

ተማሪው ምን መማርእንዳለበትና መምህሩም ምን ማስተማር

እንዳለበት የሚጠቁም የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን ለማዘጋጀት

ጠቃሚ የሆነና አንድ ወጥ የሆነ የቋንቋ ትምህርትለማዳረስ የሚረዳ

የግምገማ ዘዴን በማመላከት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ቁልፍ ሰነድ ነው፡፡

### 2.1.3 **የቋንቋ መርሃ ትምህርት አይነቶች**

የቋንቋ መርሃ ትምህርት አይነቶችን Nunan (1998፣52) እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

#### 2.1.3.1 **ሰዋስዋዊ መርሃ ትምህርት**/grammatical syllabus/

Nunan (1988 ፣ 28) ሰዋስዋዊ መርሃ ትምህርት በአሁኑ ሰአት ግልጋሎት እየሰጠ ያለና አደረጃጀቱም ከቀላል ወደ ዉስብስብ አካሄድ ስልት የተከተለ ሆኖ የመጀመሪያው ቀጣዩን ለማወቅ መሰረት የሚሆን የህጎች ስብስብ የሚበዛበት በመሆኑ ይህ መርሃ ትምህርት ዉስብስቡን የቋንቋ ባህርይ ለመግለጽ አለመቻሉ ድክመት ይታይበታል በማለት ይገልጻሉ፡፡

#### 2.1.3.2 **ግልጋሎታዊ ወይም እሳቤያዊ መርሃ ትምህርት** /functional national syllabus

(Nunan 1988፣ 24 Finocciaro እና Brumfit 1983) በመጥቀስ ግልጋሎታዊ ወይም እሳቤያዊ መርሃ ትምህርት ግልጋሎታዊ አቅምን እነደመነሻ የሚወስደው የቋንቋው ተናጋሪ ለተግባቦት ተግባር እንዴት? መቼ ? እና ዬት? ቋንቋውን ይጠቀማሉ በሚለው ላይ ያተኩራል፡፡

ግልጋሎታዊ መርሃ ትምህርት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንዳሉት Nunan (1988) ዘርዝረዋቸዋል፡፡

※ ተጨባጭ የትምህርት ተግባራትን ያሰባሰበ ነው፣

※ ቋንቋዉን ከክፍል ዉጪም ባለው መስተጋብር ያገለግላል፣

※ ለማዳመጥና ለማንበብ ክሂሎች ትኩረት ይሰጣል፣

※ ከውስጥ የመነጨ የመግባባት ስሜትን ይፈጥራል፣

※ ከነበረው የመማር ማስተማር ስልት ወጣ ብሎ በተፈጥሮ ሊዳብር የሚችልና

※ የዉጭ ቋንቋዎችን በስፋት እንዲስፋፋ የሚጠቅም ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ይህ መርሃ ትምህርት ከሰዋስዋዊ መርሃ ትምህርት የተሻለ ነው ቢባልም እንደ Nunan (1988፣ 37) በዚህ መርሃ ትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ለማስተማር የሚያገለግሉ ግብአቶች የቋንቋውን መንገዶች በአግባቡ የሚገልጹ አይደሉም በማለት መርሃ ትምህርቱ ያለበትን ድክመት አስፍረዋል፡፡

2.1.3.3 **ቅደም ተከተላዊ መርሃ ትምህርት**/procedural syllabus/

Nunan(1988፣45) (Richards,Platt,እና Weber(1985) ጠቅሰው ቅደም ተከተላዊ መርሃ ትምህርት በተግባር ላይ ያተኩራል፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በድርጊት በመተግበር ስራ ላይ እንዲያውሉ የሚያደርግ የመርሃ ትምህርት አይነት ነው፡፡

የዚህ መርሃ ትምህርት ጠንካራ ጎን ተማሪውን በማነቃቃት በተግባርና በተግባቦት ላይ ማተኮሩ ሲሆን የሚመረጡ ድርጊቶች ከክፍል ዉጭ ካለው ሁኔታ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ አለማሳየቱ ደግሞ ደካማ ጎኑ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

2.1.3.4 **ይዘት ተኮር መርሃ ትምህርት**/content based syllabus/

እንደ Nunan (1988፣48) አገላለጽ የይዘት ተኮር መርሃ ትምህርት በዋናነት መሰረት የሚያደርገው ከቋንቋ ዉጭ በሆኑ በሌሎች እንደ ሳይንስና መሰል የትምህርት አይነቶች

ላይ ነው፡፡ዋና ትኩረቱም በቋንቋ ሥርዓት ላይ ሳይሆን ቋንቋን በመጠቀም የትምህርት ሂደትን ምቹ የሚያደርግ የመርሃ ትምህርት አይነት ነው፡፡

### 2.1.4 **የቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘት አመራረጥ**

ስለ ቋንቋ ትምህርት ይዘት አመራረጥ ተስፋዬ (1981፣37) "የቋንቋ መርሃ ትምህርት በሚዘጋጅበት ወቅት በተማሪው ላይ እንዲመጣ የተፈለገው ለውጥ የሚጠቁሙ ዓላማዎች ከተቀረጹ በኋላ ቀጣዩ ሥራ ይህን ዓላማ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ይዘት መምረጥ ነው፡፡" ይዘቶቹ ሲመረጡ ደግሞ የተነደፉትን ዓላማዎች የማስገኘት ብቃታቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ተስፋዬ (1981፣40) ለቋንቋ ትምህርት የሚመረጡ ይዘቶች በሚመረጡበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ሁኔታዎች እንዳሉ ከዚህ በታች እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

ሀ. ተማሪው መለማመድ ያለበት ወደ ታቀደው ዓላማ የሚያደርሰውን ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ መሰረት ለቋንቋ ትምህርት የሚመረጡ ይዘቶች ከተቀረጸ ዓላማ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት/ተጣጥሞሽ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ለ. የትምህርት ይዘቱ ተማሪው ተግባራዊ ሊያደርገው የሚችል መሆን አለበት፡፡

ሐ. የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች አንድ ዓይነት አላማን ለማስጨበጥ ይችላሉ፡፡

መ. አንድ የትምህርት ይዘት በርካታ ዓላማዎችን ከግብ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ይህም ማለት የትምህርቱ ይዘት አንድ ብቻ ሆኖ በተማሪው ላይ የሚያስገኘው የባህሪይ ለውጥ ከአንድ የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

አለም (1995፣26) በቋንቋ ትምህርት ይዘት መረጣ እንደመስፈርት የሚታዩ ነጥቦች እንደሚከተለው አስቀምጧል፡-

ሀ. የቋንቋ ትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ የቋንቋውን ተማሪ ዕድሜ፣

የዕዉቀት ደረጃ፣የአካባቢ ሁኔታ፣ፍላጎት፣ ወዘተ በትኩረት እየተጠና ሊሆን ይገባል፡፡እነዚህን ጉዳዮች ያላጤነ የይዘት መረጣ የቋንቋ ተማሪዎችን አላስፈላጊ ችግር ዉስጥ ከመክተቱም በላይ የታቀደውን ዓላማ በጭራሽ ከግብ ሊያደርስ አይችልም፡፡

ለ. የቋንቋ ትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ የተነደፈዉን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማ ግብ ለማድረስ የሚችል መሆን አለመሆኑ እየታየና እየተመረመረ ሊሆን ይገባል፡፡ዓላማን የዘነጋ፣ዓላማን መሰረት ያላደረገ ይዘት መረጣ ወደአልተፈለገ አቅጣጫ ሊመራ ስለሚችል ምንጊዜም ቢሆን ይዘት ሲመረጥ ዓላማ እየታሰበ መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሚመረጡበት ወቅት የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ ከግብ የሚያደርሱና የተማሪውን ፍላጎት፣ችሎታና ዳራ መሰረት ማድረግ አለባቸው፡፡

### 2.1.5. የቋንቋ መርሀ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

አላማዎች ከተነደፉና የትምህርት ይዘቶች ከተመረጡ በኋላ ቀዓ ሎ □ሚመ□□ ቶ□ዱ፣ የተመረጡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ይዋቀሩ □ጁም ጁ□ራፃ □ሚለ□ ዓ□ቒ ይከተላል ተስፋዬ( 1981፣ 41)፡፡

ስለዚህ አላማውን ከግብ ያደርሳሉ ተብሎ በተመረጡ ይዘቶች አማካኝነት ይመጣል ተብሎ □ሚታሰበ□ □ባህሪ ለ□ዓ በተፅባር ጁታይ ዘንድ የተመረጡ ይዘቶች በጥሩ

ሁኔታ ሊደራጁ ይገባል፡፡ ለትምህርት ይዘቶች አጥጋቢ በሆነ ስልት መዋቀር ስኬት ሶስት ዋና ዋና ጉዳዩች መሟላት እንዳለባቸው Tyler (1949፣ 84-85) እንደሚከተለ□· ጹቶልነሉ፡፡

**ሀ.ተከታታይነት (Continuity)**

ተከታታይነት የሚለው እሳቤ የአንድን ትምህርት ቀጣይነት ያመለክታል፡፡ ተከታታይነት በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ አንድ አይነት ዕውቀት ለማስገኘት ወይም ለማሳደግ ሲባል በተደጋጋሚ የሚመጣ የትምህርት ይዘት ነው፡፡ አንድ ትምህርት ተከታታይነት አለው ሲባል የትምህርቱ የመጨረሻ ክፍል ከቀጣዩ ትምህርት መግቢያ ጋር ግንኙነት አለው ማለት ነው፡፡

**ለ.ተለጣጣቂነት (Sequence)**

ተለጣጣቂነት የሚለው የይዘት አደረጃጀት እሳቤ ከተከታታይነት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በዚህ እሳቤ መሰረት የአንድ ይዘት በትምህርት ውስጥ መደጋገም ብቻ ሳይሆን የትምህርቱ ይዘት ቀድሞ ከቀረበበት ጥልቀት ወይም ክብደት በሰፋ ሁኔታ በቀጣዩ ትምህርት ላይ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ በአጠቃላይ የተማሪው የትምህርት ደረጃው እያደገ ሲሄድ የሚቀርብለት የትምህርት ይዘት ስፋትና ጥልቀቱ እየጨመረ መሄድ ይኖርበታል፡፡ ተስፋዬ(1981፣40)፡፡

**ሐ. ቅንጅት (Integirity)**

ቅንጅት (ተዋህዶ) በትምህርት ይዘቶች መካከል ያለው ግንኙነት፣ □እርስ በርስ መደጋገፍን የሚያመለክት ነው፡፡ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ይዘቶችም የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ሃሳብ ተስፋዬ(1981፣41) የትምህርት ልምዶች (ይዘቶች) የእርስ በርስ መ□ፉቶኡ፣ የትምህርት ልምዶች አንዱ ሌላውን የማዳበር እና የማበልፀግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

2.1.5. ***የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ***

#### 2.1.5.1 **የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነት**

ለመማር ማስተማሩ ስራ ክንውን በጽሁፍ ከሚቀርቡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ዋነኛው ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ስለ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት ትምህርት ሚኒስቴር (1994፣14) "መማሪያ መጽሐፍና አብሮት የሚመጣው የመልመጃ መጽሐፍ በሥርዓተ ትምህርቱ ተጠቅሶ የቀረበውን ትምህርት አብዛኛው የሚሸከረከርበት ማዕከላዊ ጉዳይ ነው" በማለት ይገልጻል፡፡

Ur (2006፣183) ስለመማሪያ መጽሐፍ ምንነት ሲገልጹ "መማሪያ መጽሐፍ የምንለው በአንድ የትምህርት አይነት ዉስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ይዘቶችን የሚይዝ ነው፡፡ይህም መምህሩም ሆነ ተማሪዉ ሊከተሉት የሚገባቸውን መርህ የሚያመላክትና ለቋንቋ ትምህርት ወሳኝ የሆነ የማስተማሪያና የመማሪያ መሳሪያ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

ተስፋዬ (1981፣96) "የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ፣ዕድሜና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተወሰነ ክፍል ማስተማሪያነት የሚያገለግል መሳሪያ ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡

Massoud, እና Raheleh.(2011፣ 62) መማሪያ መጻሕፍት በዓለም ላይ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ዉስጥ ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡አያይዘዉም የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እድገትና ከፍተኛ ጥራት ያላቸዉ ቁሳቁሶች መፈጠር ለአዳዲስ የመማሪያ መጽሐፍት በየአመቱ መጨመር ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበዉ የምሁራን ገለጻ ለመረዳት እንደሚቻለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉት የመማሪያ መጻሕፍት ምንጫቸው የመርሃ ትምህርት እንደሆነ፣ተማሪዎች በሚማሩባቸው የክፍል ደረጃዎች ሁሉ ምን ምን ይዘቶችን መማር እንዳለባቸው በውስጣቸው አካተው የያዙ አገልግሎታቸው ላቅ ያለና በየጊዜው ዘመኑ የሚያፈራቸውን አዳዲስ ፈጠራዎችን ባለውና በነበረው ላይ እያከሉና እያሳደጉ፣እየተሻሻሉና እየተስፋፉ የሚሄዱ ትልቅ የማስተማሪያ መሳሪያ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

#### 2.1.5.2 **የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ጠቀሜታ**

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣሉ፡፡ ይህን በማስመልከት ትምህርት ሚኒስቴር (1994፣4) እንደሚከተለዉ ይገልጻል፡፡

ሀ .በመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ ተማሪው ይማረዋል ተብሎ የተቀመጠውን ይዘት በተለያዩ መንገዶች እንዲማሩ ያደርጋል፡

ለ. መምህሩ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት በሚፈልግበት ጊዜ ማተኮር ያለበት በየትኛውይዘት ላይ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ሐ. ቢተነተኑ በጣም ዝርዝር ሊሆኑ የሚችሉ የይዘት እሳቤዎችን ወይም መረጃዎችን ሰብስቦና አጠር አድርጎ ያቀርባል፡፡

መ. የመማሪያ መጽሐፍት በቂ ስልጠና ያላቸውና የታላሚው ቋንቋ ትምህርት ችሎታያላቸው መምህራን በሌሉበት እንደ ርቀት ትምህርት ባለ ሁኔታ ተማሪው በራሱ መማር እንዲችል ይረዳል፡፡

ሠ. ከክፍል ዉጭ አመቺ በሆነ ቦታና ጊዜ የትምህርት ሥራውን ለመቀጠል ያስችላል፡፡

ረ. ለብዙ ተማሪዎች ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት ደረጃ / ዕውቀት ይሰጣል፡፡

ሰ. ለመምህሩ ትምህርቱን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት መንገድ ያሳያል፡፡

ሸ. ሥዕል፣ሠንጠረዥ እና ካርታ የመሳሰሉ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል፡፡

ቀ. ማለማመጃ ጥያቄዎችን ያካትታል፡፡

በ. መምህሩ የሚያስተምርበትን የማስተማሪያ መሳሪያዎች በመፈለግና ይረዳል፡፡

በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲያውል

በአጠቃላይ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት በተለያዩ አካባቢዎች የሚማሩ ተማሪዎች ተመሳሳይ ዕውቀት እንዲኖራቸው የማድረግ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም በላይ ለመምህሩ የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ጥልቅ ሀሳቦችን አካቶ የያዘና የተለያዩ መረጃዎችን ያቀፈ በመሆኑ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

## 2.1.5.3 **የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አይነቶች**

አሰቴር ግርማ (2007፣13) Grant (1987፣ 12) ጠቅሳ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በሁለት እንደሚከፈሉ በመግለጽ እነሱም ጥንታዊ የመማሪያ መጻሕፍት (traditional text books) እና ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት (communicative text books) እንደሚባሉ አስፍራለች፡፡

### 2.1.5.3.1 **ጥንታዊ የመማሪያ መጻሕፍት** (traditional text books)

ጥንታዊ የመማሪያ መጻሕፍት የሚባሉት በቋንቋ መዋቅር ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡እነዚህ መጻሕፍት ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስውና ስርዓት እንዲያውቁ የሚያስገድዱ በመሆናቸው በታላሚው ቋንቋ በሚገባ ለመግባባት እንዳይችሉ ያደርጋሉ፡፡

### 2.1.5.3.2 **የጥንታዊ መማሪያ መጻሕፍት ባህርያት**

እንደ አሰቴር (2007፣14) የጥንታዊ መማሪያ መጽጻህት የሚከተሉት ባህርያት አሏቸው፡፡

※ ከቋንቋ ተግባቦት ይልቅ ለሰዋስውና ለቅርጽ ትኩረት ይሰጣሉ፣

※ ከማዳመጥና ከንግግር ክሂል ይልቅ ለንባብና ለጽህፈት ክሂል ትኩረት ይሰጣሉ፣

※ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለመተርጎሚያነት ይጠቀማሉ፣

※ በቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ ለቋንቋ አጠቃቀም ቅድሚያ ይሰጣሉ፣

※ የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ትኩረት በመርሃ ትምህርትና በፈተናዎች ላይ ስለሆነ

ለመምህሩ፣ለሥራና ለፈተና ዝግጅት ቀላል በመሆናቸው በመምህሩ ዘንድ ተወዳጅ ናቸው፡፡

**2.1.3.5.2 ተፅባቦታዊ የመማሪያ መፃሕፍት (Communicative text books)**

ተፅባቦታዊ የመማሪያ መፃሕፍት በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባቦታዊ የመማር ሁኔታዎችን በማቅረብ በቋንቋው መግባባት የሚችሉበትን ሁኔታዎች የሚያመቻቹ የመማሪያ ዓይነቶች ናቸው:: ዓላማቸው በጥንታዊ □መማሪ□ መፃሕፍት ላይ የታዩ ችግሮችን በመቅረፍ የቋንቋ ትምህርት ክፍሉን ለተግባቦት ምቹ ማድረግ ነው::

Grant (1987፣14) ስለተፅባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት ባህሪያት የሚከተለውን አስፍረዋል::

- ተማሪዎች በማህበራዊ ህይወታቸው እንዲግባቡ እ□□ □□ርፉል፤
- የተማሪዎችን ፍላጎት ያንፀባርቃሉ፤
- ከቋንቋው ሰዋስው ይልቅ በክሂሎች ላይ ያተኩራል፤
- አራቱን የቋንቋ ክሂሎች አመጣጥኖ ያቀርባሉ፤
- ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን በመሆን እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፤
- የቋንቋ ይዘቶችና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ በቋንቋው የዕለት ተዕለት አገልግሎትን መነሻ የደርጋሉ፤
- ከቋንቋው አጠቃቀም ትክክለኛነት ይልቅ ሐሳብን ለማመንጨት ቅድሚያ የሚሰጡ የመማሪያ መፃሕፍት ዓይነቶች ናቸው::

በአጠቃላይ ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት በዘመናችን ከፍተኛ ተቀባይነት እ□ዩና □መ□ □መማሪ□ መነሕአት ዓይነቶች ሲሆኑ ዓላማቸውም የቋንቋውን ሥርዓት ከማሳወቅ ጁልቅ በታላሚው ቋንቋ ተማሪዎቹ እንዲግባቡ ማድረግ ነው:: ስለዚህ ለቋንቋ ትምህርት ተፅባቦታዊ የመማሪያ መፃሕፍት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው::

## 2.1.6 የቋንቋ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት ተጣጥሞሽ

ከላይ ስለመርሃ ትምህርት ምንነትና የመማሪያ መጻሕፍት ምንነት ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን መርሃ ትምህርት በአንድ የተወሰነ ትምህርት ሊጠቃለሉ የሚችሉ የትምህርት

ይዘቶችን የሚያካትት ሲሆን መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ የተመረጡ ይዘቶች ወደ ተግባር ተለውጠው ለተማሪው የሚቀርብበት ነው፡፡

ይህንን በማስመልከት Richard (1987፣2) "መርሃ ትምህርት በተግባር ሊገለጽ የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያ የሆነ የሥርአተ ትምህርት አካል ሲሆን በተግባር የሚታየውም መገለጫው በሆነ በመማሪያ መጻሕፍት አማካይነት ሲሆን ለትምህርት ዉጤታማነትም ትልቅ ድርሻ አለው" በማለት በሁለቱ መካከል ያለውን የጠበቀ ግንኙነትና ትስስር ያስረዳሉ፡፡

Dubin እና Olishtain (1986፣29) እንደገለጹት መርሃ ትምህርት ሲዘጋጅ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ እና ጥናት ተደርጎበት ሲሆን በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት መካተት ያለባቸዉን የትምህርት ይዘቶች ይወስናል፡፡በሌላም በኩል ምን ማስተማር እንደሚያስፈልግ፣እንዴት ማስተማር እንደሚቻልና በምን መልኩ መገምገም እንደሚገባ መረጃ ስለሚሰጥ የመማሪያ መጻሕፍት በመርሃ ትምህርቱ መመራት እንዳለበት ግድ መሆኑን ያብራራል፡፡

Cunnings (1984 ፣ 5) መማሪያ መጻሕፍትና መርሃ ትምህርት ተያያዥና ተደጋጋፊ መሆን አለባቸው በማለት ሁለቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ያላቸውን ቁርኝት ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Cunnings (1984፣51) የመማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች አወቃቀርና የትምህርቱ አካሄድ የሚወሰነው በመርሃ ትምህርቱ ዓላማ መሠረት በመሆኑ ሁለቱ ተቃራኒ መሆን የለባቸውም በማለት ይገልጻሉ፡፡

የመማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጁ መርሃ ትምህርቱን መሠረት ማድረግ አለባቸው፡፡ይህ ከሆነ ነው በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጻሕፍቱ መካከል ተጣጥሞሽ አለ ሊባል የሚችለው፡፡ በዚሁ መሰረት ስለመርሃ ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት ይዘቶች መረጣ፣አደረጃጀትና በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጻሕፍቱ መካከል መኖር ስላለበት ግንኙነት ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች አጥኚው የሚከተሉትን መርሆዎች ለትንታኔው ተከተሏል፡፡

ይዘት መረጣን በተመለከተ የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ መሠረት ማድረግና አለማድረግ እና የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ ያማከለ መሆን አለመሆኑን፣የይዘቶች አደረጃጀትን በተመለከተ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን ከመከተል አንጻር እና በተከታታይ የክፍል

ደረጃ ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ደረጃን ጠብቀዉ ስፋትና ጥልቀታቸዉ እየጨመረ ከመሄድ አንጻር እንዲሁም ተጣጥሞሽን በተመለከተ መማሪያ መጻሕፍቱ በመርሃ ትምህርቶቹ ከመመራት አንጻር ከሰነድ ፍተሻውና በቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

## 2.1.7 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኚት

የዚህ ጥናት አጥኚ በ2001 ዓ.ም የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት በ2004 ዓ.ም ከታተመው የተማሪው መጽሐፍ ጋር ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ከመጀመሩ በፊት ከዚህ ቀደም ከዚሁ ርዕስ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ጥናቶች ለማየት ሞክሯል፡፡ አለም (1994፣193-194) "የ10ኛ ክፍል የቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማዎች የይዘት ግምገማ" በሚል በሰሩት ጥናት ላይ የመርሃ ትምህርት የዓላማ አቀራረጽ ችግሮች እንዳሉበት በመጠቆም የመፍትሄ ሀሳብ ናቸው ያሏቸውንም እንደሚከተለው በዝርዝር አስፍረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል አሻሚ ትርጉም ያላቸው፣ግልጽነት የጎደላቸውና ሰዋስዋዊ የቋንቋ ስህተት ያለባቸው ፣ ሊለኩና ሊመዘኑ ማለትም የተማሪውን የባህሪይ ለውጥ ለማመልከት በማይችሉ ቃላት ፣ ወዘተ የተጻፉ ዓላማዎች ጨርሶዉኑ ከመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ መወገድ እንዳለባቸው በመግለጽ የቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማ የትምህርቱን መነሻና መድረሻ ጠቋሚ በመሆኑ በዝግጅት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በመግለጽ ጥናታቸውን አጠናቀዋል፡፡ አሰቴር (2007) "በ2001) ዓ.ም የተዘጋጀው የ11ኛና የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መማሪያ መጻሕፍት ጋር ያላቸው የይዘት ዝምድና መፈተሽ" በሚል ርዕስ በሰሩት ጥናት ላይ ለሻሻሉ ይገባል ያሏቸውን ነጥቦች እነደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ይኸውም የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆችን በይዘት መረጣው ላይ አለማሳተፍ፣የይዘት አደረጃጀቱ አልፎ አልፎ ከቀላል ወደከባድ አካሄድ ያለመከተልና ጥቂት ይዘቶች ደግሞ የቋንቋ ትምህርት አደረጃጀት መርህን ያልተከተሉ እንዳሉባቸው በመጠቆም ሊሻሻሉ ይገባል ያሏቸውን በጥናታቸው ላይ አሳይተዋል፡፡

የዚህ ጥናት አጥኚ ከሁለቱ አጥኚዎች ጋር የሚያመሳስሉትና የሚያለያዩት ነገሮች አሉ፡፡ለምሳሌ ከአለም (1994) ጋር በከፊል የሚያመሳስለው በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት

ዓላማ ላይ ማተኮሩ ሲሆን፣የሚያለያየው ደግሞ የአለም ጥናት ከ14 ዓመት በፊት በነበረው መርሃ ትምህርት ላይ የተሰራና ለዚያውም የመርሃ ትምህርትን ዓላማ ብቻ የሚመለከት ሲሆን የዚህ ጥናት አጥኚ ግን ተከታታይ በሆኑ ክፍሎች ማለትም የ9ኛና 10ኛ ክፍል የመርሃ ትምህርት ዓላማና ይዘት ከተማሪው መጽሐፍ ጋር ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ ላይ ማተኮሩ እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የተፈተሸው አስቴር (2007) የሰሩት ጥናት ሲሆን ከዚህ ጥናት አጥኚ ጋር የሚያመሰስለው የይዘት ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን፣የሚያለያየው ደግሞ ዓላማና ይዘት ያላቸውን ዝምድና ዋና ዓላማ አድርጎ አለማንሳቱ ነው፡፡

ሌላኛው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያለው ሙጩ (1993) "በ1992 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለክፍል ደረጃው የቀረበው መርሃ ትምህርት የይዘት አደረጃጀታቸውና ያላቸው ዝምድና" በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናቱ ዓላማም በ1992 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ይዘት አደረጃጀትና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት አቀራረብና በመካከላቸው ያለዉን ዝምድና በምሁራን ንድፈ ሃሳብ በመታገዝ የተነተኑ ሲሆን ዉጤቱም መማሪያ መጽሐፉ በአብዛኛው መርሃ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ እንደሆነ ገልዋል፡፡በመማሪያ መጽሐፉ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ከቀረቡት መልመጃዎች ውጭ ይዘቶቹ በጥሩ ሁኔታ ተደራጅተው መቅረባቸውን በመግለጽ የመማሪያ መጽሐፉ በንግግር ይዘት ስር የታየው ክፍተት እንዲሟላ መፍትሄ በመጠቆም ጥናታቸውን አጠናቀዋል፡፡

ወንዳፈራሁ (1995) " በሀገር አቀፍ ደረጃ በ1990 ዓ.ም በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለደረጃው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ መካከል ያለ ግንኙነት" በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናታቸው ዓላማ አድርገው የተነሱትም መርሃ ትምህርቱ ለደረጃው ከተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ ይዘቶች ፣ የመማር ማስተማር ክንውኖች ፣ ግምገማዎችና ክፍለ ጊዜዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውና የሌላቸው መሆኑን መፈተሽ ነው፡፡የጥናቱን ዓላማው ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡በውጤቱም መጽሀፉ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ከቀረቡት መልመጃዎች ውጭ ይዘቶቹ በጥሩ ሁኔታ

ተደራጅተዉ መቅረባቸውን በመግለጽ የመማሪያ መጽሐፉ በንግግር የይዘት ስር የታየው ክፍተት እንዲሟላ መፍትሄ በመጠቆም ጥናቸውን አጠናቀዋል፡፡

ንጉሱ(1998) “በ1990 ዓ.ም የታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለክፍል ደረጃው በ1991 ዓ.ም ከተዘጋጀው  መማሪያ መጽሐፍ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ” በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናቱ ዓላማም “በ1990 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ዓላማና ይዘት ትንተና እና በ1991 ዓ.ም ታትሞ ለክፍል ደረጃው ከቀረበው መማሪያ መጽሐፍ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡” አጥኚው በምዕራፍ ሁለት ስለመርሃ ትምህርት ምንነት፣ስለዓላማና ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት፣ስለመማሪያ መጽሐፍ ምንነትና ዝግጅት ከምሁራን እይታ አንጻር ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡

በውጤቱም መርሃ ትምህርቱ በአብዛኛው ጥሩ በሆነ መንገድ እንደተዘጋጀ አረጋግጠዋል፡፡ሆኖም አንዳንዱ ክንውንን የማይጠቁሙና ሊለኩ በማይችሉ ቃላት የተቀረጹ ዓላማዎች መኖራቸው፣ተከታታይነታቸውን ያልጠበቁ ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ መካተታቸዉ እንደ ችግር ጠቅሰዋል፡፡በተጨማሪም መማሪያ መጽሐፉ በአብዛኛዉ መርሃ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ እንደተዘጋጀ አረጋግጠዋል፡፡ከዚህ ውጭ ስነልሳንን፣ንባብና ጽሕፈትን ከማዳረስ አኳያ በሁለቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ያለመጣጣም ችግር መኖሩን በማብራራት በመጨረሻም ለመርሃ ትምህርትና ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች በዝግጅት ወቅት ትኩረት የሚያደርጉበትን ነጥቦች በመጠቆም ጥናታቸው አጠናቀዋል፡፡

ሰሎሞን (1998) “በ1998 ዓ.ም በታተመው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማና ይዘት ትንተና” በሚል ርዕስ ዓላማ አድርጎ የተነሳው በክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ከዓላማ አነዳደፍና ከይዘት አወቃቀር መርሆች አንጻር መዘጋጀቱን መፈተሽ ነው፡፡የይዘት ትንተና ስልትን ተጠቅመው ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈ ሀሳቦች መነሻነት ስለመርሃ ትምህርት ምንነት ፣የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አነዳደፍና የይዘቶች አደረጃጀት መሰረት በማድረግ ትንታኔ አድርገዋል፡፡በዉጤቱም የመርሃ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች በጥሩ ሁኔታ የተቀረጹ እንደሆኑና ይዘቶቹም የእርስ በርስ መደጋገፍ እንዳላቸዉ አረጋግጠዋል፡፡እንደችግር የገለጹት አንዳንድ ዓላማዎች የትምህርት

ክንውንን የማይገልጹና ሊለኩ በማይችሉ ቃላት የተቀመጡ ዝርዝር ዓላማዎች መኖራቸዉን በመጠቆም ጥናታቸውን አጠናቀዋል፡፡

ከላይ ቅኚት የተደረገባቸው ሥራዎች የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን በተመለከተ የሙጩ አሻግሬ፣የወንዳፈራሁ ወልደሃናና ንጉሱ ደሳለኝ የተተኳሪዎች የክፍል ደረጃ ቢለያይም በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ማተኮራቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡፡

የሰሎሞን አይናለም ሥራን በተመለከተ የጥናቱ ዋና ዓላማ በመርሃ ትምህርቱ አላማና ይዘት ላይ ያተኮረና የመማሪያ መጽሐፍን በንጽጽሮሽ አለመመልከቱ ከዚህ ጥናት የተለየ አድርጎታል፡፡የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ጋር ያለው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ መፈተሽ የሚል ኣላማ ይዞ የተነሳ ሲሆን ከሌሎች አጥኚዎች ሥራ የሚለየው በ2001 ዓ.ም ተሻሽለው በተዘጋጁ መርሃ ትምህርቶችና ይህንኑ መርሃ ትምህርት መሠረት አድርገው በ2004 ዓ.ም በታተሙ መማሪያ መጽሐፍትና በሁለት ተከታታይ የክፍል ደረጃዎች ላይ ማተኮሩ ከሌሎች ልዩ ያደርገዋል፡፡

አጥኚው ከላይ የቀረቡትን ጥናቶች ገምግሞ እንደድክመት የተመለከታቸው ነገር ቢኖር ጥናታቸው ከርዕሰ ጉዳያቸው ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ሲጠቅሱ፣ጥናቱን ለመሥራት የተከተሏቸውን ዘዴን ግን አለማንሳታቸው ፣ እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳብ ናቸው ያሏቸውን አለመዘርዘራቸዉ እንደድክመት ለማየት ችሏል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

ጥናት ለማካሄድ የመረጠው ዘዴ በገላጭ ምርምር ዘዴ ሥር የሚታቀፈውን የዓላማና የይዘት ትንተና ስልት ነው፡፡ ያለው (2004፣21) "ገላጭ የምርምር ዘዴ ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ነባራዊ ሁኔታን መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚቀርብበት መንገድ ነው፡፡" ይላል፡፡ አጥኚውም በዚሁ አይነታዊ የምርምር ስልት በመጠቀም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩትን ዝርዝር ዓላማና ይዘቶች ለመተንተንና ለመገምገም ሞክሯል፡፡

### 3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለ9ኛና 10ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በክፍል ደረጃዎቹ ከተዘጋጁት የመማሪያ መጽሐፍት ጋር ያላቸው የዓላማና የይዘት

ተጣጥሞሽ መፈተሽ ሲሆን ይህንን ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በቀዳሚነት ለመረጃ ምንጭነት የተመረጠው የሰነድ ምርመራ ሲሆን፣ሰነዱም በ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ መጨረሻዎቹ ገጾች ላይ የሚገኙ መርሃ ትምህርቶችና የተማሪው መጽሐፍት ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠው ዘዴ ደግሞ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተመረጠው የሰነድ ምርመራውን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ነጻ ጥያቄዎች ቋንቋውን ለሚያስተምሩ መምህራን በማቅረብ ይበልጥ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው ሊመረጥ ችሏል ፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.2.1. የሰነድ ምርመራ

ለዚህ ጥናት በዋናነት የመረጃ መሰብሲቢያ መሳሪያ የሚሆነው የሰነድ ምርመራ ሲሆን ሰነዱም የሚገኘው ለጥናቱ በተመረጡ የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ማለትም የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና የተማሪው መጽሐፍ ዓላማና ይዘት ይሆናል፡፡የሰነድ ምርመራው የሚካሄደዉ በየምዕራፉ ያሉትን የመርሃ ትምህርቱንና የመማሪያ መጸሐፉን ዓላማና ይዘት ለይቶ በሠንጠረዥ በማደራጀት ተጣጥሟቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ይበልጥ ስራውን ተጨባጭ ለማድረግም ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ጥናቶች ተፈትሿል፡፡

### 3.2.2. ቃለ መጠይቅ

አጥኚው ይህን ጥናት ሲያካሂድ የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ሲሆን የቃለ መጠይቁም ይዘት የጥናቱን ዋና ዓላማ መሰረት አድርጎ የመርሃ ትምህርቱ ዓላማና ይዘት ከተማሪው መጽሐፍ አደረጃጀት ጋር የሚሄድ መሆን አለመሆኑን ለቃለ ምልልሱ ለታጨት መምህራን ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃ የሚሰበስብ ሲሆን በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ የሚሳተፉት አካላትም በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ከአሥር ዓመት ያላነሰ ያስተማሩ በገቺ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣በበደሌ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣በእንግቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣በደምቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና በቦረቻ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚያስተምሩ 15 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተመርጠዋል፡፡

ለዚህ ጥናት ቃለ ምልልስ የታጨት መምህራን የተመረጡበት ዋና ምክንያት ከመርሃ ትምህርቱም ሆነ ከተማሪው መጻፍሕት ጋር የዕለት ከዕለት ተራክቦ ስላላቸው፣እንዲሁም ለመማር ማስተማር ሥራ ዝግጅት በሚያደርጉበት ጊዜ ችግሩ በቀጥታ የሚያጋጥማቸው መሆኑ ስለሚታወቅ ከማንም በላይ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡

### 3.2.3 የትምህርት ቤት ናሙና መረጣ

አጥኚው  በጥናት አካላይነት የመረጣቸው አምስት ትምህርት ቤቶች ማለትም፤ የገቺ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣የበደሌ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣የእንግቢ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤የደምቢ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤትና የቦረቻ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ 16 መምህራን  በጠቅላይ የንሞና ዘዴን በመጠቀም  የመረጠ ሲሆን፤ትምህርት ቤቶቹም የተመረጡበት ምክንያት ከቦታ ርቀት አንጻር ሲታዩ ቅርብ በመሆናቸው ጭምር ነው፡፡

### 3.2.4 **የመረጃ ትንተና**

ያዴሳ (2007፣107)  "የመረጃ ትንተና ማለት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥንቃቄና በጥልቀት መመርመርና ማየት ሲሆን የመረጃ ፍች /ትርጎማ መስጠት/ ማለት ደግሞ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶችና መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን ማጠናቀርና መተንተን እንዲሁም መረጃዎች ምን አንድምታ እንዳላቸውና እንደሌላቸው ማሳያነው"በማለትይገልጻሉ፡፡

በዚሁ መሰረት የመረጃ ትንተናው የሚከናወነው ለ9ኛና 10ኛ ክፍል የተዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍት ይዘቶች አቀራረብ የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ መሰረት ማድረግ አለማድረጋቸው ፣ የተማሪውን ዕውቀትና ዳራ አገናዝቦ የተዘጋጁ መሆን  አለመሆናቸው እንዲሁም ጎናዊና ተዋረዳዊ የይዘት አወቃቀራቸው፣ተከታታይነታቸው፣ ተለጣጣቂነታቸውና ተጣጥሞሻቸው ምን እንደሚመስል ከሰነድ ምርመራውና በቃለ ምልልስ የተገኙትን መረጃዎች በተዛማጅ ጽሑፎችና በቀረቡት ንድፈ ሀሳባዊ ምልከታዎች መሠረትነት በሠንጠረዥ እያደራጀና እያስተያየ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የይዘትና ውጤት ትንተና

ስለመርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍት ይዘቶች መረጣ፣አደረጃጀትና በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፍቱ መካከል መኖር ስላለበት ግንኙነት ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች አኳኘው የሚከተሉትን መርሆዎች ለትንታኔው ተከተሏል፡፡

ይዘት መረጣን በተመለከተ የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ መሠረት ማድረግና አለማድረግ እና የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ ያማከለ መሆን አለመሆኑን፣የይዘቶች አደረጃጀትን በተመለከተ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን ከመከተል አንጻር እና በተከታታይ የክፍል ደረጃ ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ደረጃን ጠብቀዉ ስፋትና ጥልቀታቸዉ እየጨመረ ከመሄድ አንጻር እንዲሁም ተጣጥሞሽን በተመለከተ መማሪያ መጽሐፍቱ በመርሃ ትምህርቶቹ ከመመራት አንጻር ከሰነድ ፍተሻውና በቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ

መሠረት በማድረግ እነ (Tayler, እነ Richard, እና ዓለምና እና ተስፋዬ) በተባሉ ምሁራን ንደፈ ሃሳብ በማካገዝ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

## 4.1 የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች አጭር መግለጫ

የ9ኛና የ10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች የተዘጋጁት በ2001 ዓ.ም በሃገር አቀፍ ደረጃ ሲሆን እነዚህ መርሃ ትምህርቶች በየክፍል ደረጃዉ በተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያ የመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ ይገኛሉ፡፡ በውስጣቸውም በየምዕራፉ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ዓላማዎች፣ የቋንቋ ማስተማሪያ አዉደ ርዕስ፣ ይዘት፣ የክህሎት ብቃት፣ የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሳሪያ፣ ማጣቀሻና ግምገማን አካተው ይዘዋል፡፡ የ9ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት 63 አጠቃላይ፣ 134 ዝርዝር ዓላማዎችና 131 ዝርዝር ይዘቶች ያሉት ሲሆን የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ደግሞ 72 አጠቃላይ ዓላማዎች 123 ዝርዝር ዓላማዎችና 119 ዝርዝር ይዘቶች አሉት፡፡

የቋንቋ መርሃ ትምህርት ይዘቶች በሚመረጡበት ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉትን ዓላማዎች ማሳካት እንዳለባቸውና የሚመረጡትም ይዘቶች የተማሪውን ዳራ፣ችሎታና ፍላጎት ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው ተስፋዬ (1981) ገልጸዋል፡፡በዚሁ መሠረት ለ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት የተመረጡት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት፣ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የተማሪውን ዳራና ዕውቀት ያገናዘበ መሆኑና ለቋንቋ ይዘት መረጣ የተቀመጠውን መርህ ተከትለው የተደራጁ መሆን አለመሆናቸው በዚሁ ምዕራፍ በቀረቡት መረጃዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 4.1.2 ይዘቶቹ በ9ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት የተቀረጹትን ዓላማዎች ከማሳካት አንጻር4.1.1 የ9ኛ ክፍል የቋንቋ መርሃ ትምህርቶች የይዘት አመራረጥ

ለ9ኛና ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ዉስጥ የተካተቱት ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉትን ዓላማዎች የሚያሳኩ መሆን አለመሆናቸው በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፍቱ የተደራጁትን ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ለመተንተን ይቻል ዘንድ በአሥሩም ምዕራፎች የሰፈሩትን ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች በአራቱ ክሂሎችና በሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች ስር የተደራጁትን ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ተሳክቶ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ አንድ፡ የ9ኛ ክፍል የመርሃ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች፤ዝርዝር ዓላማዎችን ከማሳካት አንጻር

| ክፍል | ዝርዝር ዓላማዎች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|---|
| ምዕራፍ 1 | ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ውይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ | የቋንቋ ምንነት |
| | ከምንባቡ የወጡ ሐረጋትን በራሳቸው አባባል ያብራራሉ | ዘዬና ተግባቦት |
| | ከሚያዳምጡት ጽሑፍ በምክንያትና ውጤት የተገለጹ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይይዛሉ | መደበኛና ኢ-መደበኛ ቋንቋን የሚገልጽ የሚደመጥ ጽሑፍ |
| ምዕራፍ2 | የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሀሳባቸውን ይገልጻሉ | የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተል |
| | ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮችን ተጠቅመው ጭውውት ይጽፋሉ | ጭውውትን መጻፍ |
| | የምዕላድን ምንነት በምሳሌ አስደግፈው ያስረዳሉ | የምዕላድ ምንነት |
| | የሚቀርብላቸውን ግጥም የአነባበብ ስልቱን ጠብቀው ያነባሉ | የግጥምና የዝርው የአነባበብ ስልት መመሪያ |
| ምዕራፍ 3 | ስለስነ-ጽሑፍ መኖር ምክንያት የሆኑ ነጥቦችን ይዘረዝራሉ | የስነ ጽሑፍ የመኖር ምክንያቶች |
| | ገለጻና ማብራሪያን አዳምጠዉ በመረዳት ሲጠየቁ ይመልሳሉ | ገለጻን አዳምጦ በመረዳት ለጥያቄዎች መልስ መስጠት |

| | | |
|---|---|---|
| | የውይይትመመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ | የውይይት መመሪያ |
| | ሥርዓት ነጥቦችን ተጠቅመው ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ | የስርዓተነጥቦችአጠቃቀም(ድርብ ሰረዝና ነጠብጣብ) |
| ምዕ 4 | ወንድማማቾቹ የሚል አጭር ለቦለድ አንብበው ይረዳሉ | አንድ አጭር ለቦለድ |
| | የሚነበብላቸውን ጽሁፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ | አጭር ጽሑፍ |
| | ክርክር ያካሂዳሉ | - |
| | አጣማሪዎችን በመጠቀም የተጣመሩ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ | በአያያዥ ቃላት እንዲያያዙ የተጠየቀላቸው ዐ.ነገሮች |
| | ግሶችን ከግስ ይመሰርታሉ | ሌሎችግሶች የሚመሰረቱባቸው ግሶች |
| | ዘይቤዎችንና ፈሊጣዊ ንግግሮችን የለያሉ | ተቀላቅለውየቀረቡዘይቤያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች |
| ምዕራፍ 5 | የስንኞችንና ሀረጎችን ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ ያብራራሉ | ስንኞች |
| | ግጥምን ወይም ዝርው ጽሁፍን አጥንተው በቃል ያቀርባሉ | በቃል የሚጠናና መልዕክቱ የሚነገር ግጥም ወይም ዝርው ጽሑፍ |
| | ከዐ.ነገር ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ለይተው ያወጣሉ | ባለቤት፣ተሳቢናማሰሪያአንቀጽ ተለይተው የሚወጡላቸው ዐ.ነገሮች |
| | ከግጥም ውስጥ ሙያዊ ቃላትን ይለያሉ | በዘይቤ የታገዙ ግጥሞች |
| ምዕራፍ 6 | አንድ ጽሑፈ-ተውኔት አንብበው በጽሑፈ ተውኔት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ይመልሳሉ | ጽሑፈ ተውኔት |
| | የተውኔት አለባውያን ምንነት በሚመለከት ይወያያሉ | የተውኔትአለባዉያንን የሚመለከት ውይይት |
| | ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያገለግል የሥራ ደብዳቤ ይጽፋሉን | አያያዥ ቃላት በመጠቀም የስራ ደብዳቤ መጻፍ |

| | | |
|---|---|---|
| | መደብ፣ጾታና ቁጥር አመልካች የእርባታ ቅጥያዎች ይለያሉ | የእርባታ ቅጥያዎች |
| | ግጥምን ወደ ተውኔት በመለወጥና በማስፋት ወደ ጽሑፈ ተውኔት ለውጠው ይተውናሉ | ትወና |
| ምዕራፍ 7 | የቃላትን አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ | አገባባዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው የሚነጻጸርላቸው ቃላት |
| | ለጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ይሰጣሉ | የባለሙያ አስተያየት |
| | ማስታወሻ በመያዝ በራሳቸው አባባል ጽፈው በንባብ ያቀርባሉ | አስረጂ ድርሰትና አስተዋጽኦ |
| | ጭውውት ያደርጋሉ | ጭውውት |
| | ግሶችን ለአ.ነገር ክፍት ቦታዎች፣በሚስማሙ መልክ አስተካክለው ያስገባሉ | ምድባቸው ከግስ ያል ክፍል የሆኑ ቃላት |
| | ምሳሌያዊ ንግግሮችን ያሰባስባሉ | - |
| ምዕራፍ 8 | በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ | የግጥምና የዝርው የአነባበብ ስልት መመሪያ |
| | ከሚሰጣቸው ጽሑፍ ውስጥ የመሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ይለያሉ | መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን የያዘ ጽሑፍ |
| | በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብ ይወያያሉ | ለመወያያ የሚያገለግሉ ርዕሶች |
| | ዐ.ነገሮችን በስማዊና በግሳዊ ሐረጎች ይከፍላሉ | የዐ.ነገር አይነቶችን የሚያብራራ ጽሑፍ |
| | ከመገናኛ ብዙሃንና ከአካባቢያቸው የተለያዩ የዘፈን ግጥሞችን ይሰበስባሉ | የስነ-ቃል አሰባሰብን የሚያመለክቱ ነጥቦች |
| ምዕራፍ9 | በቀረበው ምንባብ ለተመሰረቱ ቃላትና ሐረጎች ፍቺ ይሰጣሉ | -- |

| | | |
|---|---|---|
| | የቀረበላቸውን ዝግጅት አንብበው የቃል ንግግር ያካሄዳሉ | ለንግግር መነሻ የሚሆን ጽሑፍ |
| | በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የጎደሉትን ሥርዓተ ነጥቦች ይሞላሉ | ሥርዓተ ነጥቦቹ ያልተሟሉለት አንቀጽ |
| | ባለንብረት አመልካች፣ባለቤትና የተሳቢ አመልካች ምዕላዶችን የያዙ ዐ.ነገሮችን ይመሠርታሉ | ዐ.ነገሮች የሚሠሩባቸው ቃላት |
| | የተለያዩ ቅኔዎችን ኅብረ-ቃል በመለየት ሰምና ወርቃቸውን ይገልጻሉ | የቅኔን ምንነት የሚገልጽ ማብራሪያ |
| ምዕራፍ 10 | ቃላትን በትክክለኛ አውዳቸው በማስገባት አንቀጽን ያሟላሉ | ያልተሟላ አንቀጽን ለማሟያነት የቀረቡ ቃላት |
| | ሙግት ይሟገታሉ | ለመሟገቻ የሚያገለግል የምንባቡ ክፍል |
| | ጠብቀውና ላልተው ሲነገሩ(ሲባሉ)የተለያየ ፍች የሚሰጡ ቃላትን ከምንባቡ ያወጣሉ | በምንባቡ ዉስጥ የሚገኙ የመጥበቅና የመላላት ድምጽ ያላቸው1 ቃላት |
| | የቅኔዎችን ህብረቃል፣ሰምና ወርቅ ይለያሉ | ቅኔዎች |

ከላይ የቀረበው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመርሃ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ለትንታኔ የተመረጡት ሙሉ አሥር ምዕራፎች ሲሆን እያንዳንዱ ዝርዝር ዓላማና ይዘት ከአራቱ የክሂልና ከሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች አንዳንድ ዓላማና ይዘት በመውሰድ የተመረጡት ዝርዝር ይዘቶች፤ዝርዝር ዓላማዎቹን ለማሳካት የቻሉ ስለመሆናቸው የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ለምሳሌ በመርሃ ትምህርቱ ምእራፍ አንድ "የቋንቋ ምንነት" ለሚለው ይዘት የተነደፈው ዓላማ "ስለ ቋንቋ ምንነት ካነበቡት ዉይይት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ"ይላል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ ከምዕራፍ 2-10 ላይ ያሉት "የስነቃል ምንነት፣የውይይት መመሪያ፣በአያያዥ ቃላት እንዲያያዙ የተጠየቀላቸው ዐ.ነገሮች፣ በዘይቤ የታገዙ ግጥሞች፣ጽሑፈ ተውኔት፣አስረጂ ድርሰትና አስተዋጽኦ፣የዐ.ነገር አይነቶችን የሚያብራራ ጽሑፍ፣ስርዓተ ነጥቦች ያልተሟሉለት አንቀጽ እና ያልተሟላ አንቀጽን ለማሟያነት የቀረቡ ቃላት " ለሚሉ ይዘቶች "ስለ ስነቃል ምንነትና ባህርያት ይናገራሉ ፣የውይይት መመሪያን ተከትለው በሚቀርቡላቸው ርዕሶች ላይ ይወያያሉ፣ አጣማሪዎችን በመጠቀም የተጣመሩ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ፣ከግጥም ዉስጥ ዘይቤዎችን ለይተው ያወጣሉ፣የተውኔት አለባውያን ምንነት በሚመለከት ይወያያሉ፣ማስታወሻ በመያዝ በራሳቸው አባባል ጽፈው በንባብ ያቀርባሉ፣ዐ.ነገሮችን በስማዊና በግሳዊ ሐረጎች ይከፍላሉ፣ከቀረቡት ጽሑፍ ዉስጥ የጎደሉትን ስርዓተ ነጥቦች ይሞላሉ፣ቃላትን በትክክለኛ አውዳቸው በማስገባት አንቀጽን ያሟላሉ " የሚሉ ግብ መች የሆኑ ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈውላቸው ይገኛል፡፡

ከላይ በምሳሌው ለማሳየት እንደተሞከረው አብዛኛዎቹ የመርሃ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘቶች የተነደፉላቸውን ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት የሚችሉ መሆናቸው በሰንጠረዡ ለማየትና ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዚሁ መሰረት ለዚህ ክፍል በሠንጠረዡ ላይ ለማሳየት ከተሞከረው 50 ዝርዝር ይዘቶች መካከል ሃምሳዎቹም የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ በተገቢው ሁኔታ የሚያሳኩ ሆነው ተገኝቷል፡፡ይህም ማለት ዝርዝር ይዘቶቹ ከዝርዝር ዓላማዎቹ የመነጩ መናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ ሁለት፡ ዝርዝር ይዘቶቹ የ10ኛ ክፍል የመርሃ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችን ከማሳካት አንጻር

| ምዕራፍ | ዝርዝር ዓላማዎች | ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|---|
| ምዕራፍ 1 | በምንባቡየቀረቡመረጃዎችንና እውነታዎችን ይመዝናሉ | የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት |

| | | |
|---|---|---|
| | ስለ ቋንቋ አጀማመርና ባህርያት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ዉይይት ያካሂዳሉ | በቋንቋ አጀማመር ላይ በተሰጡ መላምቶች ላይ ያተኮሩ የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች |
| | አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ | አማርኛ ከሌሎች አገርኛ ቋንቋዎች የተዋሳቸው ቃላት |
| | ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡ | በቃል በንባብ የሚቀርብ ጽሑፍ |
| | የቃላትን ነጻና ጥገኛ ምዕላድ ይለያሉ | ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን የያዙ ቃላት |
| ምዕራፍ 2 | ስለ ዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ ዓይነቶችና የሰው ልጅ የሚያልፍባቸውን የህይወት ዑደቶችን በቅደም ተከተል ከምንባቡ የተረዱትን ይዘረዝራሉ | የዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ |
| | | |
| | ከቃላት ሐረጋትን ይመሰርታሉ | በቃል ክፍሎች ሐረጋትን መመስረት |
| | ቃላዊ ግጥሞችን በመሰብሰብ ለክፍል ያቀርባሉ | ቅኔን(ዘይቤን)መፍታት |
| ምዕራፍ 3 | አጭር ልቦለድ ከረጅም ለቦለድ የሚለይበት ዋና ባህርያት የተገነዘቡትን ያስረዳሉ | አንብበው የተረዱትን ፍሬ ሀሳብ መናገር |
| | በረጅም ልቦለድ ዉስጥ በምልልስ መልክ የቀረበውን ክፍል ወስደው ጭውውት ማድረግ | - |
| | በአንቀጽ ዉስጥ የቀረበን ዋናሀሳብ ከሁለት ባልበለጡ ዐ.ነገሮች አሳጥረው ይጽፋሉ | የአንቀጽ ቅርጾችን ለይቶ አንቀጽ መጻፍ |
| | ተራና ዉስብስብ ዐ.ነገሮችን ይለያሉ | ተራና ዉስብስብ ዐ.ነገሮች መለየት |
| | የአንድ ረጅም ልቦለድ አንብበው የጭብጡንና | ጭብጥና መቼት መለየት |

| | | |
|---|---|---|
| | የመቼቱን ምንነት ይለያሉ | |
| ምዕራፍ 4 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ | ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት |
| | የቅስቀሳ ጽሑፍ ይጽፋሉ | የቅሰቀሳ ንግግር ጽፎ ማቅረብ |
| | “ኤድስ” በሚል ርዕስ መምህራቸው ከሚያነቡላቸው ጽሑፍ እያዳመጡ ማስታወሻ ይይዛሉ | መምህሩየሚያነብቡትን እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ |
| | የዐ.ነገር ስልትን ተመርኩዘው ዐ.ነገሮችን ይመሠርታሉ | - |
| ምዕራፍ 5 | ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ተመስርተው ዉይይት ያካሂዳሉ | የጥንድ ዉይይት |
| | ስለ ቀና አመለካከት ጠቀሜታ ንግግር ያቀርባሉ | የቀና አመለካከት ጠቀሜታ አስመልክቶ ንግግር ማቅረብ |
| | ሐረጋትን በዓይነታቸው ይመድባሉ | ስማዊ፣ቅጽላዊ፣መስተዋድዳዊ፣ግሳዊ ሐረግን ለይቶ መመደብ |
| | የተለያዩ ዘይቤዎችን ያካተቱ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ | እንቶኔ፣ምጸትና ግነት ዘይቤን በጽሑፍ ዉስጥ ተጠቅመው ዐ.ነገሮችን መመስረት |
| ምዕራፍ 6 | የግጥም ዓይነቶችን ለይተው ይናገራሉ | የግጥም ዓይነቶች |
| | በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ግጥሞችን ከተለያየ የመረጃ ምንጭ ሰብስበው በንግግር ያቀርባሉ | ግጥማዊ ስነቃሎች |
| | በግጥም ዓይነቶች ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት፣መርዘምና ማጠር ባህርይ ያላቸውን ቃላት ይለያሉ | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት |
| | በተሰጣቸው ርዕስ ላይ አጠር ያለ ግጥም ይጽፋሉ | - |
| ምዕራፍ 7 | ከምንባቡ ዉስጥም ሆነ ከሌላ ቃላትን ሰብስበው መዝገበ ቃላት ተጠቅመው ፍቻቸውንይሰጣሉ | የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች(ቀጥተኛ ፍች) |
| | በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ጭውውቶችን | በአረጋውያን የተለያዩ ተግባራት |

| | | |
|---|---|---|
| | በማዳመጥ የሚተላለፈውን መልእክት በግለ-ገለጻ ያቀርባሉ | ላይ ያተኮሩ ጭውውቶች |
| | በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዐ.ነገር ይሰራሉ | የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች |
| | አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተጠቅመው ሥላዊ ድርሰት ይጽፋሉ | ሥዕላዊ ድርሰት |
| ምዕራፍ 8 | ከምንባቡዝርዝር መረጃዎችን በመውሰድ ማብራሪያ ይሰጣሉ | ባህል ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ |
| | ሴቶች በባህል ውስጥ ያላቸውን ሚና ለይተው ይናገራሉ | በሴቶችና ባህል ላይ ያተኮሩየክርክር ርዕሰ ጉዳዮች |
| | የሴቶችን ጥንካሬ በተመለከተ የቅስቀሳና ማነቃቂያ ጽሁፍ አዘጋጅተው ያቀርባሉ | የቅሰቀሳና ማነቃቂያ ጽሁፍ |
| | የተለያዩ የዐ.ነገር አይነቶችን ለይተው ይገልጻሉ | የአ.ነገር ስልቶች |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ 9 | ስለ ሱስ ምንነትና ጉዳት በተለይ የመጠጥ ሱስን መጥፎ ገጽታ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ | የሱስ ጎጂ ገጽታ |
| | ሱስን ማቆም ይቻላል ወይስ አይቻልም በሚል ርዕስ የክርክር መመሪያን ተከትለው ይከራከራሉ | በሱስ ላይ ያተኮሩ ርዕሰ ጉዳዮች |
| | ዐ.ነገር ስልቶችን ተከትለው ዐ.ነገር ይመሰርታሉ | የዐ.ነገር ስልቶች |
| | ስለሱስ አጭር ግጥም ይጽፋሉ | በተመረጠ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚጻፍ ግጥም |

| | | |
|---|---|---|
| | መሥራት በሚያስገኘው ጠቀሜታ ላይ ከተለያዩ ማህበራት ያገኙትን መረጃ በማጠናቀር ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ | በሥራና ምርት ላይ ያተኮሩ የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች |
| | አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ስራና ምርትን | አያያዥ ቃላትን በመጠቀም |

| | በተመለከተ አንቀጽ ይጽፋሉ | አንቀጽ መጻፍ |
| --- | --- | --- |
| | የተጓደሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ያሟላሉ | |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በመርሃ ትምህርቱ ምዕራፍ 1-10 ላይ የሰፈሩት ይዘቶች ሰመረመሩ " የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት፣የጽሑፍ ንግግር ማድረግ፣የአጭርና ረጅም ልቦለድ ንጽጽር፣መምህሩ የሚያነቡትን እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ፣እንቶኔ፣ምጸትና ግነት ዘይቤን በጽሑፍ ዉስጥ ተጠቅመው ዐ.ነገሮችን መመስረት፣የግጥም ዓይነቶች፣ስዕላዊ ድርሰት፣የቅስቀሳና ማነቃቂያ ጽሑፍ፣የሱስ ጎጂ ገጽታ እና በስራና ምርት ላይ ያተኮሩ የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች" ለሚሉ ይዘቶች የተነደፉት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ "በምንባቡ የቀረቡ መረጃዎችንና እውነታዎችን ይመዝናሉ፣በምሳሌያዊ አነጋገሮች መነሻነት ንግግር ያደርጋሉ፣ስለ ረጅም ልቦለድ ቅርጽና ይዘት ከአጭር ልቦለድ ቅርጽና ይዘት ጋር ያነጻጽራሉ፣ኤድስ በሚል ርዕስ መምህራቸው ከሚያነብቡላቸው ጽሑፍ እያዳመጡ ማስታወሻ ይይዛሉ፣የተለያዩ ዘይቤዎችን ያካተቱ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ፣የግጥም ዓይነቶችን ለይተው ይናገራሉ፣አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተጠቅመው ስዕላዊ ድርሰት ይጽፋሉ፣የሴቶችን ጥንካሬ በተመለከተ የቅስቀሳና ማነቃቂያ ጽሁፍ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፣ ስለ ሱስ ምንነትና ጉዳት በተለይ የመጠጥ ሱስን መጥፎ ገጽታ አንብበው የተገነዘቡትን ያስረዳሉ፣መስራት በሚያስገኘው ጠቀሜታ ላይ ከተለያዩ ማህበራት ያገኙትን መረጃ በማጠናቀር ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ" የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን እንዳሳኩ ከዚህ በላይ በቀረቡ ማስረጃዎች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ከዚህ በተለየ ሁኔታ የመርሃ ትምህርቱ ሲመረመር እንደ ክፍተት ከታዩት መካከል በገጽ 82 ላይ "በረጅም ልቦለድ ዉስጥ በምልልስ መልክ የቀረበውን ክፍል ወስደው ጭውውት ማድረግ" የሚል ዓላማ መሰል ዐ.ነገር ተቀርጾ እናገኛለን፡፡ከዓላማ ቀረጻ መርህ ዉጭ የቀረበ በመሆኑ ይህ የትምህርት ዓላማ የተማሪውን የወደፊት ዓላማና አቅጣጫ ጠቋሚ እንዳልሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ካሉት አስር ምዕራፎች መካከል ባሉ ዝርዝር ዓላማዎችና ዝርዝር ይዘቶች መካከል በምዕራፍ አራት ገጽ 85 ላይ የሰፈረው ዝርዝር ዓላማ "የዓረፍተ ነገር ስልትን ተመርኩዘው ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ" ለሚለዉ የተመረጠ ዝርዝር ይዘት በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በተማሪው መጽሐፍ ላይ ሰፍሮ አልተገኘም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በመርሃ ትምህርቱ ምዕራፍ 6 ገጽ 93 ላይ የቀረበው ዝርዝር ዓላማ "በተሰጣቸው ርዕስ አጠር ያለ ግጥም ይጽፋሉ" የሚል ሲሆን የተቀመጠለት ዝርዝር ይዘት በመርሃ ትምህርትም ሆነ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለመመልከት አልተቻለም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በገጽ 85 እና 93 ላይ የቀረቡት ዝርዝር ኣላማዎችን አስመልክቶ የይዘቶቹ ምርጫ ለመምህሩና ለተማሪው የተተወ ነው እንዳይባልም በመምህሩ መምሪያ ላይ የተሰጠ አንዳችም ፍንጭ ባለመኖሩ ክፍተቱ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው በተለየ ሁኔታ በምዕራፍ 8 ገጽ 101 ላይ " የተለያዩ ዐ.ነገር አይነቶችን ለይተው ይገልጻሉ" ለሚለው ዓላማ የተመረጠው ይዘት " የዐ.ነገር ስልቶች " የሚል ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው ይዘት ዓላማዉን ማሳካት ቀርቶ ፈጽሞ ሊገናኝ የማይችል እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የዐ.ነገር አይነቶች (ተራና ውስብስብ) እና የዐ.ነገር ስልቶች ደግሞ (ሀተታዊ፣ትዕዛዛዊ፣ጥያቄያዊና አጋናኝ) የተለያዩ በመሆናቸው አንደኛው የሌላኛው ዓላማም ሆነ ይዘት ሊሆን እንደማይችል በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተረፈ ግን በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ላይ የቀረቡት ዘርዝር ይዘቶች ዝርዝር ዓላማዎችን በተገቢው ሁኔታ ለማሳካት የቻሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

#### 4.1.3 መርሃ ትምህርቱ የተማሪዎችን ሁኔታ ግምት ዉስጥ ያስገቡ ከመሆናቸዉ አንጻር

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሚመረጡበት ወቅት የተማሪዉን ዳራ፣ችሎታና ፍላጎት መሠረት ማድረግ እንዳለባቸዉ አለም (1995፣26/ሀ) ገልጸዋል፡፡የመርሃ ትምህርት በባለሙያዎች ጥናት ላይ ተመስርቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጅ በመሆኑ ይዘቱ

የሁሉንም ክልል ተማሪዎች  ዳራና ችሎታ በአብዛኛው ያማከለ ነዉ ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ገጽ 74 ላይ "የቋንቋ አጀማመርና መሠረታዊ ባህርያት" በሚል የተመረጠዉ ይዘት ተማሪዎች በ9ኛ ክፍል ትምህርታቸዉ ላይ "የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት" የሚል ተያያዥነት ያለዉ ይዘት ተምረው አልፈዉታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በየምዕራፉ ያሉት ይዘቶች በጎናዊም ሆነ በተዋረዳዊ አደረጃጀታቸው ለምሳሌ በ9ኛ ክፍል "የቃላት ቀጥተኛ ፍች "የሚለው ይዘት በሦስት የተለያዩ ምዕራፎች ላይ ተደራጅቶ እናገኛለን፡፡ከዚህም ሌላ "ዉይይት ማካሄድ፣የቃላት አገባባዊ ፍች፣የመሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት፣ወዘተ" ሶስት ሶስት ጊዜ በድግግሞሽ ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ይዘቶች በ10ኛ ክፍል ላይም ሰፍረዉ እናገኛቸዋለን፡፡ለምሳሌ "ዉይይት አራት ጊዜ፤የቃላት ቀጥተኛ ፍች ሁለት ጊዜ፣አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ሶስት ጊዜ፣ወዘተ" ቀርበዋል፡፡ ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው ተመሳሳይ ይዘቶች ከዚህ ቀደም ባሉት ምዕራፎችም ሆነ በተከታዩ ክፍል ውስጥ መገኘት አንዱ ለአንዱ መሰረትና ተምረዉት ያለፉት በመሆኑ ይዘተቹ ሰፋና ዘርዘር ብሎ ከመቅረባቸው ባለፈ እንግዳ ወይም አዲስ ርዕስ አይሆንባቸዉም፡፡ይህ የሚያሳየው የ10ኛ ክፍል ትምህርት ይዘቶች የ9ኛ ክፍል ትምህርትን ይዘት መሠረት አድርጎ የተመረጠ በመሆኑ መርሃ ትምህርቱ የተማሪዉን ዳራ ያገናዘበ ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን በ9ኛ ክፍል የተመረጡ ይዘቶች በ10ኛ ክፍል ላይ ሰፋና ዘርዘር ብለው ቀርበውበታል፡፡ለምሳሌ በ9ኛ ክፍል በገጽ 78፣89፣93፣101 እና 107 ላይ የሚገኙት ቃላዊ ግጥሞች፣ምሳሌያዊ ንግግሮችንና ዘይቤዎች ለ10ኛ ክፍል ተመሳሳይ ይዘቶች መሠረት የሆኑ በመሆናቸው አዲስ አይሆኑባቸውም፡፡ይህ ደግሞ የመርሃ ትምህርቱ የተማሪውን ዳራ ያገናዘበ ብቻ ሳይሆን አደረጃጀቱ ሰፋና ዘርዘር እያለ ቀለል ካለ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ከባድ የይዘት  አካሄድ ተከትሎ የተደራጀ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በተጨማሪም የመርሃ ትምህርቱ የይዘት አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ስልት የሚከተሉ መሆናቸውን የሚከተሉትን ጥቂት ምሳሌዎችን ወስደን እንመልከት፡፡ ለትንታኔያችን ይመች ዘንድ በመጀመሪያ ደረጃ በ9ኛ ክፍል በተደራጁ አስሩም ምዕራፎች

ውስጥ ለምሳሌ የቃላት አውዳዊ ፍቺ ወይም አገባባዊ ፍቺ የሚለው በአምስት ምዕራፎች ማለትም በምዕራፍ(1፣3፣4፣7 እና 10) ውስጥ በይዘትነት ተመርጦ የምናገኝ ሲሆን የክብደት ደረጃውን በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ገጽ 7 ላይ የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል

ምሳሌ አንድ፡- 1. ወፍጮው ስለተበላሸ ጤፉን ሸረከተው፡፡

ፍች፡- ገረደፈው፣ከካው

2. አጥሩ ላይ የነበረው ምስማር የጫልቱን ቀሚስ ሸረከተው፡፡

ፍች፡- ቀደደው፣ተረተረው

3. ወታደሩ ጠላቱን በሳንጃ ሸረከተው ፡፡

ፍች፡- ወጋው

"ሸረከተው" የሚለው ቃል በሦስቱም ዐ.ነገሮች ውስጥ የተለያዩ ፍቺዎችን ወክሏል፡፡

ከላይ የቀረበውን ምሳሌ 1 ለይተን ስንመለከት "ወፍጮው ስለተበላሸ ጤፉን ሸረከተው" ለሚለው ትርጓሜ ከሸረከተ በፊት የገባው (ወፍጮው ስለተበላሸ…) የሚለው ሐረግ የተበላሸ ነገር መልካም ነገር ያስገኛል ተብሎ ስለማይታሰብ ፍችው በቀላሉ ጤፉ ሲፈጭ አለመድቀቁን ተማሪው እንዲገምት ረድቶታል፡፡

ምሳሌ ሁለት፡- በተማሪው መጽሐፍ ምዕራፍ 3 ገጽ 39 ላይ የቀረበው የአውዳዊ ፍች

አቀራረብ ከምሳሌ አንድ ሁኔታ በተለየ አቀራረብ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህንኑ በምሳሌ ለማስረዳት ይቻል ዘንድ የመልመጃውን ትዕዛዝ አስቀድመን ወደ ጥያቄዎቹ እናምራ

ትዕዛዝ፡-በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ እየተሰመረባቸው ለቀረቡ ቃላት አገባባዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ በሰጣችሁት ፍች መሠረት የራሳችሁን ዐ.ነገር መሥርቱ፡፡

ምሳሌ፡- በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት እንመለከታለን፡፡

አገባባዊ ፍች፣ ክፍል

ዐ.ነገር፡- በዚህ ክፍል ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት

እንመለከታለን፡፡

ከላይ በምዕራፍ አንድ የቀረበው የአውዳዊ ፍች (ትርጓሜ) በምዕራፍ ሦስት ከቀረበው ቀለል ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ ሦስት የተጠየቀው ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ ማለትም የቃሉ አውዳዊ ፍችና በተሰጠው ፍች ደግሞ መልሶ ዐ.ነገር ሥራን የሚጠይቅ በመሆኑ በዚህ ምዕራፍ የቀረበው መልመጃ ከምዕራፍ አንድ የበለጠ ይከብዳል፡፡

ምሳሌ ሦስት፡- በምዕራፍ አራት ላይ የቀረቡት ቃላት ዘወትራዊ ባለመሆናቸው የግድ

አውዱን ሊያሳዩ የሚችሉ ተጨማሪ ንባብን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ምሳሌ 1. ያንርብኛል 4. ጭርንቁስ

2. ታዳሚ 5. እርር ብሎ

3. አምቧረቀ 6. አሞካሻቸው

እነዚህን ቃላት ስንመለከት በጥያቄ አቀራረቡና መልሱን ለመፈለግ የሚደረገው ሥራ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከቀረቡት ምሳሌዎች ከበድ ያለ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

ስለዚህ በ9ኛ ክፍል የቀረበው የመርሃ ትምህርት አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ የአካሄድ ስልትን የተከተለ መሆኑን ምሳሌዎቹ ያስገነዝቡናል፡፡

ሌላው የይዘት አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ስልት ይዞ መደራጀቱ የተፈተሸው የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ነው፡፡በዚህ ከላይ በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የተመረጠው ይዘት በተመሳሳይ ሁኔታ የቃላትና ሐረጋት አገባባዊ ፍች ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

በ10ኛ ክፍል የቃላትና ሐረጋት አገባባዊ ፍች በሁለት ምዕራፎች ላይ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ እነዚህም ይዘቶች በምዕራፍ (2 እና 6) ላይ ይገኛሉ፡፡የእነዚህን ይዘቶች የክብደት ደረጃ በሚከተሉት ምሳሌዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ትዕዛዝ፡- ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዐ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍች ፈልጉላቸው፡፡

ሀ. መደበኛ ባህላዊ ጋብቻ በብሔረሰቡ <u>ወግ</u> እና ደንብ ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ነው፡፡

ለ. ከቤተ-ዘመድና ከጎረቤት ጋር ተማክሬ መልሱን እነግራችኋለሁ በማለት <u>ይሸኟቸዋል፡፡</u>

ሐ. ጠለፋ ልጁ ልጅቷን ይዟት <u>ሲኮበልል</u> የሚከሰት ነው፡፡

መ. ወዳ የመጣች ልጃገረድ <u>አግረ እርጥብ</u> ስለሆነች በረከት ይዛ ትመጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡

በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ምሳሌዎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍችያቸውን ለመረዳት ስለቃላቱ ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጋትን መመርመር ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ ተለምዷዊ የቋንቋ አጠቃቀምና ስለፈሊጣዊ ቃላት ትርጓሜ መጠነኛ ግንዛቤ የሚጠይቅ በመሆኑ በ9ኛ ክፍል ከቀረቡት ተመሳሳይ ይዘቶች ከበድ ያለ ነው ማለት

ይቻላል፡:ሌላው በዚሁ የክፍል ደረጃ የቀረበው ተመሳሳይ ይዘት በተማሪው መጽሐፍ ምዕራፍ 6 ገጽ 85 ላይ ያለው ሲሆን የቃላቱ አውዳዊ ፍች የተመሰረተው ከግጥም በወጡ ቃላት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

ቃላቱም የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ዐዋይ
2. ጨፌ
3. ባድማ
4. አደባባይ
5. አንጀቱን አርሰው
6. ትቢያ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የተዘረዘሩት ቃላት ከግጥም የተውጣጡ ቃላት ናቸው፡፡እንደሚታወቀው የግጥም ሥንኞች የሚዋቀሩት ተራ ወይም ዘወትራዊ በሆኑ ቃላት ሳይሆን በምርጥና እምቅ ቃላት የሚገጠም በመሆኑ አገባባዊ ፍቻቸውን ለመረዳት ለተማሪው ቀላል አይሆኑም፡፡ በዚህም የተነሳ በ10ኛ ክፍል በምዕራፍ ሁለት የቀረበው የግጥም ይዘት ለመረዳት መጠነኛ የቃላት ዕውቀትንም የሚጠይቅ በመሆኑ ከዚህ ምሳሌ ቀደም ብለው ከቀረቡት የቃላት አውዳዊ ፍች የበለጠ አዳጋች ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በትንታኔዉ ላይ የቀረቡት አስረጅዎች እንደሚያመለክቱት በ9ኛ ክፍልም ሆነ በ10ኛ ክፍል የተዋቀሩት ሌሎች ይዘቶችም ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ስልትን ተከትለው የተደራጁ በመሆናቸው እንግዳ ሆነው ለተማሪዎች ግርታን እንዳይፈጥሩ ተደርገው መደራጀታቸው የተማሪውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ አስገብተው የተደራጁ እንደሆኑ ማሳያዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.4 **የመርሃ ትምህርቱ የይዘት አደረጃጀት**

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸዉ ከይዘት መረጣ ቀጥሎ የሚመጣዉ ተግባር ይዘቶችን ማደራጀት ሰሆን Tyler (1949) ለይዘቶች በአጥጋቢ ሁኔታ መዋቀር ተከታታይነት፣ተለጣጣቂነትና ቅንጅት ዋነኞቹ እንደሆኑ ገልጿል፡፡በዚህ ጥናት በመርሃ ትምህርቶቹ ዉስጥ የተመረጡ ይዘቶች አደረጃጀት ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት አንጻር ብቻ ተፈትሸዋል፡፡ይህ ጥናት ቅንጅት ላይ አያተኩርም፡፡ምክንያቱም ጥናቱ በ9ኛና 10ኛ ክፍል ያለውን የይዘት አደረጃጀት እንጂ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸውን የይዘት አደረጃጀት ስማይፈትሽ በቅንጅት ላይ አላተኮረም፡፡

#### 4.1.4.1 **መርሃ ትምህርቱ ተከታታይነትን ከመከተል አንጻር**

እንደ Tyler (1949) ተከታታይነት በአንድ የትምህርት ዓይነት ዕወቀት ለማስገኘት ወይም ለማሳደግ ሲባል በተደጋጋሚ የሚመጣ የትምህርት ይዘት መሆኑን ገልጿል፡፡

በዚሁ መሠረት የ9ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች በተደጋጋሚ የሚገኙባቸውን ገጾች አንድ በአንድ በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 3 በ9ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት በተለያዩ ክሂሎችና የዕዉቀት ዘርፎች የቀረቡ ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን

| የመርሃ ትምህርቱ ይዘት | የድግግሞሽ መጠን | ይዘቶቹ የሚገኙባቸው ገጾች |
|---|---|---|
| አንብቦ መረዳት | 10 | 97፣100፣106፣110፣111፣113፣117፣120፣123፣126 |
| ከመጽሐፍት፣ከመጽሔትና፣ከጋዜጦች መረጃ ማግኘት | 3 | 97፣100፣105 |
| የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ | 4 | 98፣103፣117፣126፣ |
| የቃላት አገባባዊ ፍቺ | 3 | 98፣103፣117 |
| የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 2 | 107፣123. |
| የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ | 2 | 111፣126 |
| አንድን ሀሳብ በራስ አባባል መግለጽ | 1 | 124 |
| ዉይይት ማካሄድ | 3 | 104፣114፣120 |
| ተዉኔት | 1 | 115 |
| ግጥምና የግጥም ሙያዊ ቃላት | 1 | 110 |
| የልቦለድ አላባዉያን | 2 | 108፣115 |
| የቃል ክፍሎች | 2 | 106፣117 |
| ሃረጋት | 4 | 107፣114፣117፣123 |
| መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት | 3 | 106፣111፣120 |
| ንግግር | 6 | 105፣107፣114፣117፣124፣124 |
| ጽህፈት | 7 | 104.፣104 107፣115፣117፣118፣120. |

| | | |
|---|---|---|
| ማዳመጥ | 3 | 104፣114፣121፣ |
| ሥርዓተ ነጥብ | 4 | 103፣104፣114፣123፣ |
| ክርክር | 4 | 107፣114፣118፣126፣ |
| ጭዉዉት | 5 | 98፣101፣103፣118፣121፣ |
| ማስታወሻ መያዝ | 4 | 108፣111፣117፣121፣ |
| ምክንያትና ዉጤት | 1 | 97 |
| የግልና የመስሪያ ቤት ደብዳቤ አጻጻፍ | 1 | 121 |
| የድምጽመጥበቅመላላት፣መርዘም ና ማጠር የሚያመጣዉ የትርጉም ልዩነት | 2 | 111፣126 |
| ቅጥያዎች፣ የእርባታና የምስረታ ምዕላዶች | 5 | 100፣101፣113፣124፣127 |
| ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ቃላዊ ግጥሞች | 6 | 100፣101፣108፣115፣121፣124፣ |
| የቅኔን ህብረቃል መለየትና ሰምና ወርቅ ፍቺ | 2 | 121፣125 |
| ዘይቤ(መቼት፣ተለዋጭ፣ሰዉኛና ተነጻጻሪ) | 1 | 110፣ |

ከቀረበዉ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለዉ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት የቀረቡ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎችና ገጾች ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡

ለምሳሌ አንብቦ መረዳት በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን ይኼውም ለ 10 ጊዜያት፣ጽሕፈት 7 ጊዜ፣ንግግር 6 ጊዜ፣ቅጥያዎች የእርባታና የምስረታ ምዕላዶች አምስት አምስት ጊዜ፣ማስታወሻ መያዝ፣የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ፣ሀረጋት፣ሥርዓተ ነጥብና ክርክር

የመሳሰሉ ይዘቶች አራት አራት ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን፤ከመጽሐፍት፣ከመጽሄትና ከጋዜጦች መረጃ መሰብሰብ፣የቃላት አገባባዊ ፍቺ፣ዉይይት ማካሄድ፣መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትና ማዳመጥ ሦስት ሦስት ጊዜያት እንዲሁም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ፣የለበለድ አለባውያን፣የድምጽ መጥበቅ መላላት፣መርዘምና ማጠር የሚያመጣው የትርጉም ልዩነት፣የቅኔን ህብረቃል መለየትና ሰምና ወርቅ ፍቺ ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ይዘቶች ናቸው፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በመርሃ ትምህርቱ የተደራጁት ይዘቶች አብዛኛዎቹ ተደጋግመው የቀረቡ በመሆናቸው የይዘት አደረጃጀቱ የተከታታይነትን መርህ ተከትለዋል ማለት ይቻላል፡፡

በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ ከቀረቡት 131 ዝርዝር ይዘቶች መካከል 6 ዝርዝር ይዘቶች የቀረቡት አንዴ ብቻ ሲሆን እነሱም አንድን ሃሳብ በራስ አባባል መግለጽ፣ተውኔት፣ግጥምና የግጥም ሙያዊ ቃላት፣ምክንያትና ውጤት፣የግልና የመስሪያ ቤት ደብዳቤ አጻጻፍና ዘይቤ(መቼት፣ተለዋጭ፣ሰውኛና ተነጻጻሪ) ናቸዉ፡፡እነዚህ የመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች ሲደራጁ በድግግሞሽ ያልቀረቡ በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ የተከታታይነት መርህን ያልተከተሉ መሆናቸው ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 4 በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ዉስጥ በክሂልና የዕውቀት ዘርፍነት የቀረቡ ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን

| የመርሃ ትምህርቱ ይዘት | የድግግሞሽ ብዛት | ይዘቶቹ የሚገኙባቸው ገጾች |
|---|---|---|
| አንብቦ መረዳት | 10 ጊዜ | 75፣77፣82፣85፣89፣92፣96፣100 103፣106፣ |
| ዉይይት | 5 ጊዜ | 74፣75፣86፣ 89፣100፣ |
| የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ | 2 ጊዜ | 74፣96 |
| ቃልን በምዕላድ መተንተን | 3 ጊዜ | 74፣92፣103 |
| ማዳመጥ | 7 ጊዜ | 74፣77፣85፣96፣100፣103፣106፣ |

| | | |
|---|---|---|
| እዉነታና የግል አስተያየት | 3 ጊዜ | 74፣82፣86፣ |
| መረጃ የማግኛ ንባብ | 9 ጊዜ | 74፣75፣78፣83፣86፣93፣97፣101፣106 |
| መመሪያዎችን ማንበብ | 6 ጊዜ | 75፣78፣85፣101፣103፣104፣ |
| ማስታወሻ መዉሰድ | 8 ጊዜ | 75፣78፣83፣86፣89፣93፣97፣101 |
| የቃላት አገባባዊ ፍቺ | 2 ጊዜ | 77፣92 |
| በቃል ዉስጥ የድምጽ መጥበቅ መላላት፣መርዘምና ማጠር | 2 ጊዜ | 77፣92 |
| በቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት | 5ጊዜ | 77፣89፣93፣100፣106፣ |
| ሃሳብን በራስ አባባል መግለጽ | 4 ጊዜ | 78፣92፣96፣97 |
| የጽሁፍ ንግግር | 6 ጊዜ | 78፣89፣92፣97101፣107 |
| ጭዉዉት | 3 ጊዜ | 78፣82፣96 |
| ቃላዊ ግጥሞች/የሥራ፣የፍቅር… | 2 ጊዜ | 78፣93 |
| ምሳሌያዊ አነጋገሮች | 2 ጊዜ | 78፣89 |
| ልቦለድ/ረጅም፣አጭር | 1 ጊዜጊዜ | 82 |
| የዐረፍተ ነገር አይነቶች ከመዋቅር አንጻር | 2 ጊዜ | 82፣106 |
| እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 2 ጊዜ | 82፣103 |
| አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት | 3 ጊዜ | 82፣96፣106 |
| የአንቀጽ ቅርጾች | 2 ጊዜ | 83፣103 |
| ፈሊጣዊ አነጋገር | 3 ጊዜ | 83፣86፣101 |
| ተራና ዉስብስብ ዐ.ነገሮች | 2 ጊዜ | 83፣89 |

| | | |
|---|---|---|
| ተመሳሳና ተቃራኒ ፍቺ | 2 ጊዜ | 85፣96 |
| የዐ.ነገርስልቶች/ሀተታዊ፣ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣አጋኖዊ | 2 ጊዜ | 85፣100 |
| ሥርዓት ነጥብ/ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ፣ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ/ | 3 ጊዜ | 85፣96፣103 |
| የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር | 4 ጊዜ | 85፣97፣101፣106 |
| ቃለ ጉባኤ | 1 ጊዜ | 86፣ |
| ዘይቤያዊ አነጋገር/እንቶኔ፣ምጸት፣ግነት/ | 3 ጊዜ | 89፣92፣107 |
| የግጥም ዓይነቶችና መልእክት | 4 ጊዜ | 92፣93፣97፣104 |
| ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች | 1 ጊዜ | 101 |
| ኅብረ ቃልን በመለየት ቅኔን መፍታት | 2 ጊዜ | 101፣104 |
| ክርክር | 1ጊዜ | 103 |

ከላይ ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዉስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ይዘቶች ተከታታይነት ይታይባቸዋል፡፡

በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ውይይት፣በቃል ክፍሎች ሐረጋትን መመስረት፣የጽሑፍ ንግግር፣መመሪያዎችን ማንበብ፣ማስታወሻ መውሰድ፣መረጃ የማግኛ ንባብና አንብቦ መረዳት ያሉት ይዘቶች ከአምስት እስከ አስር ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡

ቃልን በምዕላድ መተንተን፣ጭውውት፣አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት፣ፈሊጣዊ አነጋገር፣ሥርዓተ ነጥብ፣ዘይቤያዊ አነጋገር፣ሀሳብን በራስ አባባል መግለጽ፣የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግርና የግጥም አይነቶችና መልዕክት የሚሉ ይዘቶች ከሦስት እስከ አራት ጊዜያት ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡

የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ፣የቃላት አገባባዊ ፍቺ፣በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅ መላላት፣መርዘምና ማጠር፣ቃላዊ ግጥሞች/የሥራ፣የፍቅር…፣ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣የዐ.ነገር አይነቶች ከመዋቅር አንጻር፣እማሬዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣የአንቀጽ ቅርጾች፣ተራና ውስብስብ ዐ.ነገሮች፣ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ፣የዐ.ነገር ስልቶችና ህብረቃልን በመለየት ቅኔን መፍታት የሚሉ ይዘቶች ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ በመሆናቸው የይዘት ተከታታይነት መርህን ተከትለው የተደራጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሆኖም ግን ጥቂት የሚባሉት ይዘቶች ማለትም ልቦለድ፣ቃለ ጉባኤ፣ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ክርክር በመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ የተጠቀሱት አንድ አንድ ጊዜ በቻ የቀረቡ በመሆናቸው የተከታታይነትን መርህ ያልተከተሉ እንደሆኑ በሰነድ ምርመራው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አንዳንድ ይዘቶች በ9ኛ ክፍልም ይሁን በ10ኛ ክፍል የመርሃ ትምህርት ምዕራፎች ዉስጥ ተደጋግመው የመመረጣቸዉ ሁኔታ እንዴት ያዩታል ተብለው ለቃለ መጠይቅነት የተመረጡ መምህራን የሰጡት ምላሽ ተመሳሳይነት አለዉ፡፡ ይኸዉም አንድ የትምህርት ይዘት በተለያዩ ምዕራፎች ዉስጥ ተመርጦ የመቅረብ ጥቅሙ ቀዳሚው ይዘት ለተከታዩ መሠረት በመሆኑ የይዘት ተደጋግሞ መቀረብ ለተማሪው በጣም አስፈላጊ ነው በማለት ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

### 4.1.4.2 መርሃ ትምህርቱ ተለጣጣቂነትን ከመከተል አንጻር

ተለጣጣቂነት የሚለው የይዘት አደረጃጀት ከተከታታይነት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በዚህ እሳቤ መሠረት የአንድ ይዘት በትምህርት ዉስጥ መደጋገም ብቻ ሳይሆን የትምህርቱ ይዘት ቀድሞ ከቀረበበት ጥልቀት ወይም ክብደት በሰፋ ሁኔታ በቀጣዩ ትምህርት ላይ የሚቀርብበት ሁኔታ ነው፡፡ተስፋዬ (1981፣40) ተለጣጣቂነት የጉዳዩን ተደጋጋሚነት ሳይሆን የጉዳዩን እየሰፋ መሄድን የሚጠቁም እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ሠንጠረዥ 5 የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶች ተለጣጣቂነትን ከመከተል አንጻር

| በ9ኛና 10ኛ ክፍሎች ተደጋግመዉ የቀረቡ | የተደራጁበት ክፍል |
|---|---|

| የመርሃ ትምህርት ይዘቶች | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል |
|---|---|---|
| የቃላት አገባባዊ ፍቺ | በ3ምዕራፍ | በ2 ምዕራፍ |
| ቃልን በምዕላድ መተንተን | በ5 ምዕራፍ | በ3ምዕራፍ |
| የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ | በ4ምዕራፍ | በ2 ምዕራፍ |
| በቃል ዉስጥ የድምጽ መጥበቅ መላላት፣መርዘምና ማጠር | በ2 ምዕራፍ | በ2 ምዕራፍ |
| በቃል ክፍሎች ሐረጋትን መመስረት | በ4 ምዕራፍ | በ5 ምዕራፍ |
| እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | በ2 ምዕራፍ | በ2 ምዕራፍ |
| ጭውውት | በ5 ምዕራፍ | በ3 ምዕራፍ |
| አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት | በ3 ምዕራፍ | በ3 ምዕራፍ |
| ሥርዓተ ነጥቦች | በ4 ምዕራፍ | በ3 ምዕራፍ |
| ዘይቤያዊ አነጋገር | በ1 ምዕራፍ | በ3 ምዕራፍ |
| የግጥም አይነቶችና መልእክት | በ1 ምዕራፍ | በ2 ምዕራፍ |
| ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች | በ4 ምዕራፍ | በ1 ምዕራፍ |
| ህብረ ቃልን በመለየት ቅኔን መፍታት | በ2 ምዕራፍ | በ2 ምእራፍ |
| ክርክር | በ4 ምዕራፍ | በ1 ምዕራፍ |

በ9ኛና በ10ኛ ክፍሎች የተደራጀዉ የይዘት ተለጣጣቂነት ሲመረመር ለምሳሌ የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ወስደን ስንመለከት በ9ኛ ክፍል ላይ የተቀመጠው በአራት ምዕራፎች ላይ ሲሆን፤ በ10ኛ ክፍል ላይ ደግሞ በሁለት ምዕራፎች ላይ ሰፍሮ እንዳለ በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆመ ቢሆንም በተግባር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የታየው ግን በአንድ ምዕራፍ ላይ ብቻ ነው ፡፡ ይሁን እንጂ የይዘቱ ተደጋግሞ አለመቅረብ ካልሆነ በስተቀር፤ የቀረቡት ይዘቶች ክብደት፣ጥልቀትና ስፋት ከምዕራፍ ምዕራፍ እንዲሁም ከክፍል ወደ ክፍል ደረጃው እያደገ ሰለመሆኑ በዚሁ ጥናት ከገጽ 38-41 የተሰጡት አስረጅዎች ለተለጣጣቂነቱ ማሳያዎች ናቸው፡፡

በሌላም በኩል በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት በቁጥር አንሰው ነገር ግን በአቀራረብ ደረጃ ጠለቅ ያለ ይዘት ያላቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከእነዚህም መካከል ቃልን በምዕላድ መተንተን፣የቃላትአገባባዊ ፍቺ፣ጭውውት፣ሥርዓት ነጥቦች፣ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ክርክር የሚሉ ይዘቶች በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ላይ በቁጥር አንሰዉ የተገኙ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የመርሃ ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አንሰው ከቀረቡት መካከል የተለጣጣቂነት ደረጃን ለማሳየት ይቻል ዘንድ በምዕራፍ አንድና በምዕራፍ ስድስት "ቃልን በምዕላድ መተንተን" የሚሉትን ይዘቶች ለአብነት ወስደን በሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበው ነጻና ጥገኛ ምዕላድን መለየት የሚመለከት ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠርዥ ስድስት፡ነጻና ጥገኛ ምዕላድ

| ተራ ቁጥር | ቃል | ነጻ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | መለኮታዊነቱን | መለኮት | -አዊ | -ነት | -ኡ | -ን |
| 2 | ተማሪዎቹን | ተማሪ | -ዎች | -ኡ | -ን | |
| 3 | መምህራኑን | መምህር | -አን | -ኡ | -ን | |
| 4 | ልጅነታችን | ልጅ | -ነት | -አች | -ን | |

በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን የምዕላድ ትንተና ደግሞ እንደሚከተለው እንመልከት

ሠንጠረዥ ሰባት፡ የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት

| ተራ ቁጥር | ቃል | ነጻ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መርከበኛ | መርከብ | -ኧኛ | ቅጽል መስራች |
| 2 | ሆዳም | ሆድ | -ኣም | ቅጽል መስራች |
| 3 | ወተታም | ወተት | -ኣም | ቅጽል መስራች |
| 4 | ጎጠኛ | ጎጥ | -ኧኛ | ቅጽል መስራች |

ከላይ በሁለቱ ሠንጠረገዦች ላይ ስለ ምዕላድ ትንተና የቀረቡት ምሳሌዎች ተለጣጣቂነት ታይቶባቸዋል፡፡ በምዕራፍ አንድ ከቀረበው ምሳሌ የምንረዳው የምዕላድን ማለትም፣የነጻና ጥገኛ ምዕላድን ምንነት ያስተዋወቀ ሲሆን፣በምዕራፍ ስድስት የቀረበው ምላድ ይዘት ደግሞ የነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን አገልግሎት የሚመለከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክብደት ደረጃቸውን ስንመለከት በሁለተኛው ሠንጠረዥ ላይ የቀረበው ከባድ ነው፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ቃልን ነጻና ጥገኛ ምዕላድ ብሎ ከመተንተን በዘለለ የነገረን አንድም ነገር የለም፡፡ በሁለተኛው ላይ የቀረበው ግን ከምዕላድ ምንነት አልፎ የጥገኛ ምዕላዶች አገልግሎትን የሚያሳይ በመሆኑ የክብደት ደረጃው ከመጀመሪያው ከፍ ያለ መሆኑ ተለጣጣቂነቱን ያመለክታል፡፡

ይህንኑ በተመለከተ ለቃለ መጠይቅ የተመረጡ መምህራን ለሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁ መርሃ ትምህርቶች ዉሰጥ የተካተቱት ይዘቶች በቁጥር አለመመጣጠን ማለትም 9ኛ ክፍል ላይ ያሉት ይዘቶች በ10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ላይ ካለዉ አንሰዉ መገኘታቸዉ ከመርህ አንጻር እንዴት ይመለከቱታል ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ደረጃ በ10ኛ ክፍል የተደራጀዉ ይዘት በ9ኛ ክፍል ላይ ከሰፈረዉ ይዘት ያነሰ ይምሰል እንጂ የይዘቱ ክብደት ስፋትና ጥልቀት ከ9ኛ ክፍል ከፍ ያለ ነዉ በማለት አሰተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ የሰነድ ፍተሻዉ እንደሚያመለክተዉ ከተለጣጣቂነት አንጻር የመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች በአብዛኛው በ9ኛ ክፍልም ሆነ በ10ኛ ክፍል ባሉ ምዕራፎች የይዘቶቹ አደረጃጀት

ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ ስልት ተከትለው የተደራጁ በመሆናቸው ተለጣጣቂነት ታይቶባቸዋል፡፡

## 4.2 የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች አመራረጥ

በትምህርት ይዘት መረጣ የሚመረጡትን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተማሪውን ወደ ተፈለገ ዓላማ የሚያደርሱ እንዲሁም በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚማር ተማሪ ዳራ፣ እድሜና የዕውቀት ደረጃ ያገናዘበ መሆን መቻል አለበት በማለት ተስፋዬ (1981) ያስረዳሉ፡፡የተማሪውን ዳራ ያላገናዘበ የመማሪያ መጽሐፍት ዝግጅት ያስገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው ውጤት ላይ  ከማድረስ ይልቅ ወደተሳሳተ አቅጣጫ በማምራት ተማሪው ትምህርቱን እንዲጠላው የማድረግ ሁኔታንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 4.2.1 የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ከማድረግ አንጻር

በ9ኛና 10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት የተመረጡት ይዘቶች በተደረገው የሰነድ ፍተሻ አብዛኞቹ የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ መሠረት ያደረጉ ስለመሆናቸው የሚከተሉት ከየክፍሉ የተወሰዱት ጥቂት የየምዕራፎቹ ዓላማና ይዘቶች ማሳያዎች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ አምስት  የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ያደረጉ ስለመሆናቸው፤

| ክፍ | የመርሃ ትምህርት ዓላማ | ገጽ | የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች | ገጽ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ል | | | | |
| 9ኛ | ስለ ቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ያገኙትን ግንዛቤ ይናገራሉ | 97 | የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት | 2-5 |
| 9ኛ | ስለስነቃል ያላቸዉን ግንዛቤ መረጃን አስደግፈዉ በንግግርና በጽሑፍ ያብራራሉ | 100 | የስነቃል አጠቃላይ ግንዛቤ/ከልዩ ልዩ ገለጻዎች፣ማብራሪያዎች… | 16-18 |
| 9ኛ | የቃላት ቀጥተኛና አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ | 103 | ለቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት | 39 |
| 9ኛ | የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ | 106 | የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 67 |
| 9ኛ | ከግጥም ዘይቤዎችን ለይተዉ ያወጣሉ | 110 | ከግጥም ዘይቤዎችን ለይቶ ማዉጣት | 90-91 |
| 9ኛ | ቃላትን እንደባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅመዉ ዐ.ነገር ይሠራሉ | 113 | ዐ.ነገር/ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ | 109 |
| 9ኛ | አስተዋጽኦ ነድፈዉ አስረጅ ድርሰት ይጽፋሉ | 118 | አስረጅ ድርሰት መጻፍ | 138 |
| 9ኛ | በዉይይትና በጭዉዉት በተሰጣቸዉ ሚና ይሳተፋሉ | 121 | ዉይይትና ጭዉዉት | 151 |
| 9ኛ | ከተለያዩ ዐ.ነገሮች ዉስጥ የሚገኙትን የስምና የግስ ሙያዎችን ይለያሉ | 123 | የሰምና የግስ ሙያዎች የሚለዩባቸዉ ዐ.ነገሮች | 155-156 |
| 9ኛ | ቅኔን ይፈታሉ | 127 | ቅኔ/ኀብረቃል፣ሰምና ወርቅ ፍቺ | 176 |
| 10ኛ | የአንድን ሀሳብ እዉነታና የግል አስተያየት ለይተዉ ይናገራሉ | 74 | እዉነታና የግል አስተያየት | 9-10 |
| 10ኛ | በቃል ክፍሎች ሃረጋትን መስርተዉ ይጽፋሉ | 77 | በቃል ክፍሎች ሃረጋትን መመስረት | 29-30 |
| 10ኛ | ፈሊጣዊ አባባሎችን ይተረጉማሉ | 83 | የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍቺ ለይቶ መናገር | 47 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10ኛ | ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸዉ ይጠቀማሉ | 85 | ትዕምርተ ጥቅስን በተገቢ ቦታ መጠቀም | 62-63 |
| 10ኛ | የተለያዩ ዘይቤዎችን ያካተቱ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ | 89 | እንቶኔ፣ምጸትና ግነት ዘይቤን በጽሑፍ ዉስጥ ተጠቅመዉ ዐ.ነገሮችን መመስረት | 74 |
| 10ኛ | በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ግጥሞችን ከተለያየ መረጃ ምንጭ ሰብስበዉ በንግግር ያቀርባሉ | 93 | ግጥማዊ ሰነቃሎች | 82 |
| 10ኛ | የቅሰቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ያደርጋሉ | 97 | የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር | 95 |
| 10ኛ | ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን ያሟላሉ | 101 | ጅምር ምሳሌያዊ ንግግር | 115 |
| 10ኛ | ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን አቀናጅተዉ ቃል ይመሰርታሉ | 103 | ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን አቀናጅቶ ቃል መመስረት | 125 |
| 10ኛ | ከተሰጠዉ ምንባብ ዉስጥ ተራና ዉስብስብ ዐ.ነገሮችን ይለያሉ | 106 | ተራና ዉስብስብ ዐ.ነገሮች መለየት | 138 |

ከላይ ከቀረበዉ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለዉ አብዛኛዎቹ የመማሪያ መጽሐፍት ይዘቶች በይዘት መረጣ ወቅት የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ መሠረት ማድረጋቸዉ ነዉ፡፡ለምሳሌ ያህል በ9ኛ ክፍል የመርሃ ትምህርቱ ዓላማ ሆኖ የቀረበዉ "ስለስነቃል ያላቸዉን ግንዛቤ መረጃን አሰደግፌዉ በንግግርና በጽሑፍ ያብራራሉ" የሚል ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት "የስነቃል አጠቃላይ ግንዛቤ" የሚል ይዘት ተመርጧል፡፡ በዚሁ የክፍል ደረጃ ባለዉ መርሃ ትምህርት በዓላማነት የቀረበዉ "በተለያዩ ዐ.ነገሮች ዉስጥ የሚገኙትን የስምና የግስ ሙያዎችን ይለያሉ" ለሚለዉ ዓላማ ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ የተመረጠዉ ይዘት ደግሞ "የስምና የግስ ሙያዎች የሚለዩባቸዉ ዐ.ነገሮች" የሚል ሆኗል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የ10ኛ ክፍልም ቢሆን ለምሳሌ " የተለያዩ ዘይቤዎችን ያካተቱ ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ" ለሚለዉ የመርሃ ትምህርት ዓላማ ማሳኪያ እንዲሆን የተመረጠዉ ይዘት "እንቶኔ፣ምጸትና ግነት ዘይቤን በጽሑፍ ዉስጥ ተጠቅመዉ ዐ.ነገሮችን መመስረት"

የሚል ተመርጧል፡፡በተጨማሪም በዚሁ ክፍል መርሃ ትምህርት በዓላማነት የተቀረጸዉ "በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ግጥሞችን ከተለያየ መረጃ ምንጭ ሰብስበዉ በንግግር ያቀርባሉ" ለሚለዉ ዓላማ "ግጥማዊ ስነቃሎች" የሚል ይዘት ተመርጧል፡፡

ከላይ እንዳየነዉ አብዛኛዎቹ የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ያደረጉ ቢሆንም ከዚህ በታች በአስረጅነት የቀረቡት የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ባለማድረጋቸዉ ያለመጣጣም ተስተወሏል፡፡

**አስረጅ አንድ**

※ ሐረግና የድምጽ መጥበቅና መላላት ማጠርና መርዘም/ከአማርኛ ዉጭ/ መርሃ ትምህርት

ምዕራፍ 5 ገጽ 110

**አሰረጅ ሁለት** የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ያላደረጉ ይዘቶች (10ኛ ክፍል)

※ በቀረቡላችሁ ቃላት አንቀጽን ማሟላት መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ገጽ 22

※ አሳጥሮ መጻፍ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ ሦስት ገጽ 39

※ የማዳመጥ ክህሎትን ማዳበር/መመሪያ/ የመማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አራት ገጽ 59

※ የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አምስት ገጽ 69 መርሃ ትምህርቱን

መሠረት አላደረገም፡፡

※ የግጥም ባህርያት ምዕራፍ 6 ገጽ 84 በመርሃ ትምህርቱ ያልተጠቀሰ ነገር ግን በመማሪያ

መጽሐፍ የተተገበረ

※ ከምንባቡ ለወጡ አባባሎች በራስ አባባል አብራርቶ መናገር መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ

ሰባት ገጽ 94 መርሃ ትምህርቱን መሰረት አላደረገም

※ በምዕራፍ 9 መርሃ ትምህርት የቀረቡ ይዘቶች በዚሁ ምዕራፍ በመማሪያ መጽሀፍ የተተገበሩ ሲሆን መርሃ ትምህርቱን መሰረት ያላደረጉ ይዘቶች አሉ

ለምሳሌ ገጽ 124 ዉይይት

ሌላዉ "ቃልን በምዕላድ መተንተን..."የሚል ይዘት ሲኖረዉ ወደ መማሪያ መጽሐፍ ሲተገበር ተቃራኒነት ይታይበታል፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ 9 ገጽ 125 ትዕዛዝ 2 ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቅጥያ ምዕላዶች እየመረጣችሁ ለነጻ ምዕላዶች(ቃላት) ተስማሚ የሚሆኑትን በመቀጠል ቃላትን

መስርቱ

ምሳሌ፡1. ልጅ (ነጻ ምዕላድ + -ኦች) = ልጆች( ከነጻና ጥገኛ ምዕላድ የተመሠረተ ቃል)

2. ሜዳ + - አማ = ሜዳማ

ከላይ የተጠቀሱትን ምሳሌ 1 እና 2 ስንመለከት 10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ላይ የቀረበው ይዘት ቃልን በነጻና ጥገኛ ምዕላድ መተንተን የሚል ሲሆን በተማሪዉ መጽሐፍ ላይ ይዘት ሆኖ የቀረበው ግን በነጻ ምዕላድ ላይ ጥገኛ ምዕላዶችን በመቀጠል ቃልን መመሥረት የሚል ሆኖ በመገኘቱ የትዕዛዝ ተፋልሶ ታይቷል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና መሠረታዊ ዓላማ በ2001 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሻሽለዉ የተዘጋጁት የ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ላይ የሰፈሩ ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች በተማሪዉ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡት ዓላማዎችና ዝርዝር ይዘቶች ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡

ከዋናዉ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሷል፡፡

1. የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማ ከማሳካት አንጻር እንዴት ይታያሉ?
2. የመርሃ ትምህርቱ ዓላማና ይዘት ከመማሪያ መጽሐፍት የይዘት አደረጃጀት ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ምን ይመስላል?

3. በ9ኛና 10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍትና መርሃ ትምህርቶች ዉስጥ ያሉት የይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዴት ይታያል?

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻዉ የተገኘዉ መረጃ እንደሚያመለክተዉ አብዛኛዎቹ የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች መሠረት ያደረጉ ናቸዉ፡፡ሆኖም ግን በመርሃ ትምህርቶቹ ዉስጥ ተጠቅሰዉ በመማሪያ መጻሕፍቱ ዉሰጥ ያልተካተቱ ይዘቶች፤እንዲሁም በመማሪያ መጻሕፍቱ የሚገኙና በመርሃ ትምህርቱ ያልተካተቱ ዓላማዎቸ አልፎ አልፎ በየምዕራፉ የታዩ ሲሆን የመልመጃዎች ትዕዛዛትና የመልመጃዎቹ አቀራረብ ያለመጣጣም ተስተዉለዉባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኞቹ የተመረጡት ይዘቶች የተማሪዉን የቀደመ ዕዉቀት ያገናዘቡ ሲሆን፤አደረጃጀትን በተመለከተ ከጥቂት ይዘቶች በስተቀር የተከታታይነትና ተለጣጣቂነት መርህን በመከተል ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ የተደራጁ ከመሆናቸዉም በላይ የየክፍል ደረጃዎቹ መማሪያ መጻሕፍት የመርሃ ትምህርቶቹን ይዘት መሠረት ያደረጉ ሆነዉ ተገኝተዋል

5.1 **ማጠቃለያ**

ጥናቱ ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሰለመርሃ ትምህርቶቹና መማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች አመራረጥ፣አደረጃጀትና በሁለቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ስላለዉ ግንኙነት ዳሰሳ አድርጓል፡፡በዚሁ መሠረት የቀረቡ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ በጥናቱ የተገኙ ዉጤቶች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

- የይዘት መረጣዎችን በተመለከተ የ9ኛና 10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶች ዉስጥ የተካተቱ ይዘቶች የመርሃ ትምህርቶቹን ዓላማ መሠረት ማድረጋቸዉና የተማሪዎችን የዕዉቀት ደረጃ ግምት ዉስጥ ከማስገባት አንጻር ጥረት መደረጉን እንዲሁም የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያገናዘቡ መሆናቸው እንደጠንካራ ጎን ይጠቀሳል፡፡

- የ9ኛና 10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍቱ ዓላማዎችና ይዘቶች የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎችና ይዘቶችን መሠረት ያደረጉ በመሆናቸዉ በሁለቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ተጣጥሞሽ መኖሩ ተስተውሏል፡፡
- አደረጃጀትን በተመለከተ የ9ኛና 10ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፍት ዉስጥ የተካተቱት ይዘቶች በአብዛኛዉ የተደራጁት የተከታታይነትና የተለጣጣቂነት እንዲሁም ከቀላል ወደ ከባድ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አካሄድ መከተላቸዉ እንደ ጠንካራ ጎን ይጠቀሳል፡፡
- በክፍል ደረጃዎቹ የመርሃ ትምህርቶቹና የመማሪያ መጽሐፍቱ ዝምድና በተመለከተ በ9ኛ ክፍልም ሆነ በ10ኛ ክፍል ባሉ ምዕራፎች ዉስጥ የሚገኙ ይዘቶች በተናጥልም ሆነ በንጽጽሮሽ ያለው ክፍተት እንደአጠቃላይ ሲታይ የጠበበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በ9ኛ ክፍልም ሆነ በ10ኛ ክፍል የሚገኙ ጥቂት ዓላማዎችና ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ ያሉና በመማሪያ መጽሐፍቱ ዉስጥ ያልተካተቱ፤እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፍቱ ዉስጥ ኖረው በመርሃ ትምህርቱ ያልተቀመጡ ዓላማዎችና ይዘቶች አልፎ አልፎ መኖራቸው ተስተውለዋል፡

## 5.2 **አስተያየት**

የመማር ማስተማሩን ሥራ የተሳካ ለማድረግ በየጊዜዉ የሚዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጽሐፍት በዝግጅት ወቅትና አገልግሎት በመስጠት ላይ እያሉ ጠንካራ ጎናቸዉ እነዲጎለብትና ደካማ ጎናቸዉ ደግሞ እነዲሻሻል ማጥናት ከመስኩ ባለሙያዎች የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

በዚሁ መሠረት በ2001 ዓ.ም በተዘጋጁ የመርሃ ትምህርቶች ላይ ተመሥርተዉ በ2004 ዓ.ም የታተሙት የ9ኛና 10ኛ ክፍል የመማሪያ መጻሕፍት በሚሻሻሉበት ጊዜ ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸውና ሊተኮርባቸዉ የሚገቡ ነጥቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

- በክፍል ደረጃዎቹ መርሃ ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፍት ውሰጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ይዘቶች የተከታታይነትና የተለጣጣቂነት መርሆችን ተከትለው የተደራጁ በመሆናቸው ለወደፊትም ተጠናክሮ ቢቀጥል፡፡
- በክፍል ደረጃዎቹ የመርሃ ትምህርቶችና የመማሪየ መጻሕፍቱ ይዘቶች ከተጣጥሞሽ አንጻር እንደ አጠቃላይ ሲታይ ተዛምዷቸው ጎልቶ ስለሚታይ በዚሁ ቢቀጥል፣
- አልፎ አልፎ ጥቂት ይዘቶች የመርሃ ትምህርትን የአደረጃጀት መርሆችን ያልተከተሉ ይዘቶች በመኖራቸው ወደፊት በመርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ ዝግጅት ወቅት ትኩረት ቢደረግ፣
- አንዳንድ ዝርዝር ዓላማዎች ይዘት ያልተመረጠላቸው ስላሉ ለወደፊት በዝግጅት ወቅት ትኩረት ቢደረግባቸው፣
- መርሃ ትምህርቱ፣የመማሪያ መጽሐፍቱና የመምህሩ መምሪያ አንዳንድ ቦታ ላይ የዝርዝር ዓላማና ይዘት አለመገናኘት የሚታይ በመሆኑ እርምት ቢደረግ፤የሚል አስተያየቱን በመስጠት ጥናቱን አጠናቋል፡፡

## ዋቢ መጻህፍት


ሙሉጬ አሻግሬ፡፡(1993)፡፡ *በ1192 ዓ.ም የታተመው የ10 ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ እና ለክፍል ደረጃው የቀረበው መርሃ ትምህርት የይዘት አደረጃጀታቸውና ያላቸው ዝምድና ለባችለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡*

*በድሩ ሀሰን፡፡(1994 )፡፡ የትምህርት ተከታታይ ምዘናና ግምገማ ጽንሰ ሀሳቦችና ቴክኒኮች፣* የጥናትና ምርምር አገልግሎት ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት፣ አዲስ አበባ

ሰሎሞን አይናለም፡፡(1998)፡፡ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዓላማና ይዘት ትንተና፣ለባችለር ድግሪ ማሟያ ቀረበ፡፡ጅማ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡(1981)፡፡ሥነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ያልታተመ፡፡

ትምህርት ሚንስቴር፡፡ (2004) ፡፡የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ፡፡ ዱባይ፣አል-ጉረር አሳታሚ ድርጅት፡፡

-------- (2004)፡፡የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህሩ መምሪያ፡፡ ዱባይ አል-ጉረር አሳታሚ ድርጅት፡፡

--------- (2004)፡፡የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፡፡ ዱባይ፣ አል-ጉረር አሳታሚ ድርጅት፡፡

--------- (2004)፡፡ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ፡፡ ዱባይ፣ አል-ጉረር አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታደሰ ሲባሞና ሌሎች፡፡(2004)፡፡አማርኛን የማስተማር ስነ ዘዴ፡፡ ትምህርት ሚንስቴር ለድህረ ምረቃ ለማስተማር ስነ ዘዴ ዲፕሎማ (post graduate diploma in teaching) መርሃግብር የተዘጋጀ ሞጁል፣አዲስ አበባ፡፡

ንጉሱ ደሳለኝ፡፡(1998)፡፡የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና ለክፍል ደረጃው በ1991 ዓ.ም በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ መካከል ያለው ተጣጥሞሽ፣ ለድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1992)፡፡*መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ፡፡*አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አስቴር ግርማ፡፡(2007*)፡፡በ2001 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሻሽለዉ በተዘጋጁት የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶችና በመማሪያ መጻሕፍት መካከል ያለዉ የይዘትዝምድና፣* ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ *ያልታተመ፡፡*

*ወንዳፈራሁ ወልደሃና፡፡(1995)፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ በ1990 ዓ.ም በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለደረጃው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ መካከል ያለ ግንኙነት፣ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ፣ያልታተመ፡፡*

ያዴሳ ቶሎሳ፡፡ (2007*)፡፡መሰረታዊ የጥናትና ምርምር ዘዴዎች*፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004*)፡፡የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Alemayehu Bishaw.(2012).*Education in Ethiopia:past,present,and future prospects*. Bahir Dar University.

Bekele and others.(2013).Principles of curriculum inquiry.Debub university,un published module.

Brumfit,Cj.& Johanson,K(eds)(1997). *The Communicative approach to language teaching.*Oxford:OUP.

Dubin and Olishtain.(1986).C*ourse design.*Cambridge; Cambridge University Press.

Grant, N. (1987). *Making the most of your text book.* London; Longman.

Hendrikz E.(1986).*Introduction to Educational psychology*. Published by macmillan education ltd.

Jack C.Richards.(2013). *Curriculum development in language teeching. Cambridge.cambridge university press.*

MoE.(2002). *Education policy.*Addis Ababa,Minstry of Education

Nunan D.(1988).*Syllabus designs.*Oxford;Oxford University press.

Parkes J and harr's, M,B.(2002,56).*The purpose of a syllabus.*CBSCO publishing, Vol.50/ No 2

White J.(1984*). The aim of education restated.*London Routdedge and kegan paulc plc.

Ur.P.(1996*). A course in language Teaching and Theories.*Cambridge University Press.

Richards, J.C. & Rodgers, T.S. (1986). *Approaches And Methods In Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

--------- (1987).*The context of language Teaching.*Cambridge; Cambridge

University press.

Wills D.(1990).*The lexical syllabus*. London and Glasgow: Collins *COBUILD.*

Tayler.(1949).*Basic principles of carriclum and instruction*.Chicago;Chicago University press.

Yalden,J.(1987).*Princeples of Course design for language teaching*.Cambridge. Cambridge University press.